# ስለኢትዮጵያ ፡ ደራሲያን ።

< åQ-Ÿ •-‘ -£

# ስለኢትዮጵያ ፡ ደራሲያን ።

ፕሮፌሰር ፡ ታምራት ፡ አማኑኤል ።

፲፱፻?? ፡ ዓ.ም

# መቅድም ።

ጽሑፉ ፡ የፕሮፌሰር ፡ ታምራት ፡ አማኑኤል ፡ ነው ። ፕሮፌሰር ፡ ታምራት ፡ ከዛሬ ፡ ኻያዐምስት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ በትምርትና ፡ ሥነጥበብ ፡ ሚኒስቴር ፡ አማካሪ ፡ ኾነው ይሠሩ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፕሮፌሰር ፡ በመባል ፡ ፈንታ ፡ ሊቀማእምራን ፡ ይባሉ ፡ ነበር ።

ትዝ ፡ እንደሚለኝ ፡ ባ፲፱፻፴፮ ፡ ዓ.ም ፡ በቱርክ ፡ አገር ፡ የሚገኝ ፡ አካዳሚ ፡ ይኹን ፡ ወይም ፡ የደራሲያን ፡ ማኅበር ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሥነጽሑፍና ፡ ስለኢትዮጵያዊያን ፡ ደራሲያን ፡ ጠይቆ ፡ ስለነበረ ፡ ጥያቄውን ፡ የመለሱት ፡ ሊቀማእምራን ፡ ታምራት ፡ አማኑኤል ፡ ነበሩ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሥነጽሑፍና ፡ ስለኢትዮጵያዊያን ፡ ደራሲያን ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ የምታመለክተውን ፡ ይህችን ፡ ጽሑፍ ፡ ሊቀማእምራኑ ፡ በዐማርኛ ፡ አዘጋጅተው ፡ አቀረቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠያቂው ፡ የውጪ አገር ፡ ድርጅት ፡ በመኾኑ ፡ መጠን ፡ መግለጫውም ፡ በውጭ ፡ ቋንቋ ፡ መዘጋጀት ፡ ነበረበት ። ስለዚህ ፡ ጽሑፉቱ በእንግሊዝኛ ፡ እንድትተረጐም ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ ጽሑፎችን ፡ በማረም ፡ ሥራ ፡ አገለግልበት ፡ ወደነበረው ፡ ክፍል ፡ ተላከች ። የፕሮፌሰሩ ፡ ዐማርኛ ፡ ጽሑፍም ፡ በዚያን ጊዜ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተርጓሚ ፡ ለነበሩት ፡ ለአቶ ፡ እንግዳ ፡ ጽጌሐና ፡ ጥቂት ፡ ከባድ ፡ ኾኖ ፡ የዐማርኛውን ፡ አስተሳሰብ በእንግሊዝኛ ፡ አስተካክለው ፡ ለመግለጥ ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለ ኾነባቸው ፡ በማስረዳቱ ፡ ሥራ ፡ እንድረዳቸው ፡ ታዝዤ ፡ ዐብረን ፡ ከሠራን ፡ በኋላ ፡ እንግሊዝኛው ፡ ሲላክ ፡ ይህ ፡ ዐማርኛው ፡ ግን ፡ እኛው ፡ ዘንድ ፡ ቀረ ።

የጽሑፉ ፡ አሰካክና ፡ አገላለጥ ፣ የታሪኩም ፡ አቀራረብና ፡ ውበት ፡ ደስ ፡ ስለሚለኝ ፡ ጽሑፉን ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ እመለከተው ፡ ነበር ። ነፍሳቸውን ፡ ይማርና ፡ በሕይወት ፡ ቢኖሩ ፡ ኖሮ ፡ ከዚህም ፡ የተሻለ ፡ ጽሑፍ ፡ ለአገራቸው ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያበረክቱ ፡ ማሳሰብ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፡ ይኾናል ። ባለመኖራቸው ፡ አልተቻለም ። ካኹን ፡ ቀድሞም ፡ 'ማህአትማ ፡ ጋንዲ' ፡ ከሚባለው ፡ በቀር ፡ በስማቸው ፡ ታትሞ ፡ የወጣ ፡ ሌላ ፡ ጽሑፍ ፡ መኖሩን ፡ አላውቅም ።

ይህችም ፡ ጽሑፍ ፡ በመጽሐፍነት ፡ ለመውጣት የሚያበቃት ፡ መጠን ፡ ባይኖራትም ፡ በኾነው ፡ መንገድ ፡ ቁምነገር ፡ ላይ ፡ ብትውል ፡ ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ለስማቸው ፡ መጠሪያ ፡ ልትኾን ፡ ትችል ፡ ነበር ፡ እያልኹ ፡ በማሰላሰልበት ፡ ጊዜ ፡ በቀዳማዊ ፡ ኀይለሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ለሚገኘው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቋንቋዎችና ፡ ሥነጽሑፍ ፡ ክፍል ፡ ብትቀርብ ፡ ለምርምርና ፡ ለጥናት ፡ ትረዳለች ፣ በመጽሔትም ታትማ ፡ ትወጣና ፡ ለፕሮፌሰሩ ፡ ዝክረ ፡ ስም ፡ ትኾናለች በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ ከሥራ ፡ ጓደኛዬ ፡ ካቶ ፡ አሰፋ ፡ ገብረ ማሪያም ፡ ጋር ፡ ከተመካከርንበት ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ተግባር ላይ ፡ እንድትውልላቸው ፡ የኒህን ፡ ታላቅ ፡ ምሁር ፡ ስምና ሥራ ፡ የምታስታውስውን ፡ ይህችን ፡ በ፷፩ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈች ትንሽ ፡ ጽሑፍ ፡ ለዚሁ ፡ ድርጅት ፡ አቀረብኋት ።

ከበደ ፡ ደስታ
፲፱፻፷፩ ዓ.ም

# ስለኢትዮጵያ ፡ ደራሲያን ።

የጥንቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አፈታሪክ ፣ አንድ ፡ ሽህ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፣ ባገራችን ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራን ፡ የነበሩበት ፡ ከዚያ ፡ ዠምሮ ፡ እስዛሬ ፡ ድረስም ፡ ሊቅ ፣ መምህርና ፡ ደራሲ ፡ አልጠፋበትም ፡ ይላል ። ቢኾንም ፡ አፈታሪኩ ፡ ሽህ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ከብሉያት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ መጻሕፍት ፡ መኖር ፡ አለመኖራቸውን ፡ አያመለክትም ። ኢትዮጵያዊው ፡ ስለሰው ፡ ዘር ፡ በጠቅላላው ፡ በተለይም ፡ ስለ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ስለሐበሻ ፡ ሕዝብ ፡ የጥንት ፡ ታሪክ ፡ የተነገረው ፡ ኹሉ ፡ ስንኳ ፡ ገና ፡ ባይመረመር ፣ ለታሪክ ፡ ምርመራ ፡ እስከዛሬ ፡ የተደከመበት ፡ ሥራ ፣ ከዚህ ፡ በላይ የተመለከተውን ፡ አፈታሪክ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ አስመስሎ ፡ ያሳየናል ። አፈታሪካችን ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ከሕዝበ እስራኤል ፡ ጋራ ፡ ግኑኘነት ፡ እንደነበረ ፣ ንግሥተ ፡ ሳባ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ (ሐበሻ) ፡ የምንለውንና ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ የደቡቡን ፡ ክፍል ፡ ትገዛ ፡ እንደነበረች ፣ ኢየሩሳሌም ፡ ድረስ ፡ ኼዳ ፡ ከሰሎሞን ፡ ጋር ፡ ተዋውቃ ፡ ከርሱ ፡ ፩ኛ ፡ ምኒልክ ፡ የተባለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ እንደወለደች ፣ ፩ኛ ፡ ምኒልክም ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ላሉት ፡ ነገሥቶቻችን ፡ አባት ፡ መኾኑን ፣ እርሱም ፡ አባቱን ፡ ሰሎሞንን ፡ ለማየት ፡ ኼዶ ፡ ከየሩሳሌም ፡ ሲመለስ ፣ ጽላተሙሴንና ፡ እስከሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ከእስራኤላዊያን ፡ የተጻፉትን ፡ መጻሕፍት (ብሉያትን) ይዞ ፡ እንደመጣ ፡ ይነገራል ። ይህን ፡ አፈታሪክ ፡ የሚነግሩ መጻሕፍት ፡ ባገራችን ፡ መጻፍ ፡ የጀመሩ ፡ ከሽ፫፻ኛው ፡ ዓመተምሕረት ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ሽህ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ለሕዝቡ ፡ ወንጌል ፡ ተሰብኮለት ፡ ነበር ። በሽ

ሀ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አሳብ ፣ በአሕዛ ብነት ፡ የነበረበትን ፡ ዘመን ፡ እንዲጠየፊው ፡ የሕዝበእስራ ኤልን ፡ መጻሕፍትና ፡ አሳብ ፡ እንዲወድ ፡ አድርጎት ፡ ስለ ነበረ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ የገዛ ፡ ታሪኩን ፡ እየዘነጋ ፡ የእስራ ኤል ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ከማለትና ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ የጻፍ ዋቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ አያቶቼ ፡ የጻፍዋቸው ፡ ናቸው ፡ ከ ማለት ፡ ደርስዋል ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ የእስራኤልና ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ግኑኝነት ፡ ኑሮዋቸው ፡ ይኾናል ፡ ቢባል ፣ ማስረጃው ፡ ስንኳ ፡ ባይገኝ ፣ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ በማለት በተቀበልነው ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ከብሉያት ፡ መጻሕፍት አንዳንዶቹ ፡ እስከኢትዮጵያ ፡ ደርሰው ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተቀብሎ ፡ የሃይማኖት ፡ ሥራ ፡ አስይ ዝዋቸዋል ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ ማስረጃው ፡ እስኪገኝ ፡ ድረስ ልብወለድ ፡ የመጣ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፡ እንላለን ። የዛሬው ፡ ዘ መን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ትምርት ፡ ቤት ፣ የቀረው ፡ ቀር ቶ ፡ ስለዐምስቱ ፡ ብሔረኦሪት(Pentateuque) ፡ ስንኳ ፡ በዛሬ ው ፡ አኳኋን ፡ ተሰብስበው ፡ ባንድነት ፡ መገኘት ፡ የጀመሩ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይለናል ። የዚህ ፡ ክርክር ገና ፡ ሳይጨረስ ፣ አፈታሪካችን ፣ መጽሐፈ ፡ ኦሪት ፡ በሰሎ ሞን ፡ ዘመን ፡ ካገራችን ፡ ደርሰው ፡ ነበር ፡ ሲል ፣ ለራሱ ፡ ክብረት ፡ በመጓጓት ፣ ታሪክ ፡ ጥሶ ፡ የተራመደ ፡ ኾኖ ፡ ይታየ ናል ። ይህም ፡ ከወገን ፡ ለጊዜው ፡ የበለጠ ፡ መስሎ ፡ የታየ ውን ፡ እየመረጡ ፡ ወገኔ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የዛሬ ፡ ሳይኾን የጥንት ፣ የኛ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በኹሉም ፡ የደረሰና ፣ ታሪክ ተመርምሮ ፡ ወሬው ፡ ትክክለኛ ፡ አለመኾኑ ፡ ሲታይ ፡ የሚ ቀር ፡ ነው ። በግሪኮች ፡ ሥልጣኔ ፡ ንጹሕ ፡ ቅንዓት ፡ ያደረ ባቸው ፡ ሮማዊያን ፡ የግሪኮች ፡ መዐርግ ፡ ተካፋይ ፡ ለመ

ኾን ፣ የኤኔአን ፡ ተረት ፡ ፈጥረዋል ። በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስለሕዝበእስራኤል ፡ የተነገረው ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ሲያሰኛቸው ከነበሩት ፡ እንግሊዞች ፣ አንዳንዱ ፡ ባለታሪክ ፣ ስደት ፡ የኼዱት ፡ የ፲ሩ ፡ ነገደእስራኤል ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ ሲል ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ሮማዊያንም ፡ ከግሪኮች ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ ቢኖራቸው ፡ ባለታሪክ ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ያመጣል ፡ እንጂ ፡ የኤኔአን ፡ ተረት ፡ መሠረት ፡ አያደርገውም ። የባለታሪክ ፡ ስምና ፡ መዐርግ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፣ በእንግሊዝ ፡ ደሴቶች ፡ ከምሥራቅ ፡ የመጣ ፡ ሕዝብ ፡ ሰፍሮበት ፡ ኑሮ ፡ ይኾናል ፡ ስንኳ ፡ ቢል ፣ አንግሎሳክሰን ፡ ያሥሩ ፡ ነገደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ አይልም ። እንደዚኸው ፡ ኹሉ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ በዐዲሱ ፡ ምርመራ ፡ አካኼድ ፡ የሚከታተል ፡ ሰው ፡ ከሐበሻ ፡ ሕዝብ ፡ የሴም ፡ ዘር ፡ መቀላቀሉንና ፡ የሥልጣኔው ፡ መሠረት ፡ ሴማዊ ፡ መኾኑን ፡ ስንኳ ቢረዳ ፣ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ ጋር ፡ ግኑኝነት ፡ እንደነበረው ፡ ባይጠራጠርበት ፣ ታሪኩን ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፣ ስለንግሥት ሳባና ፡ ስለሰሎሞን ፡ የሚነገረውን ፡ መሠረት ፡ አያደርግም ። ስለዚህም ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ መጻሕፍት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኑረው ፡ እንደኾነ ፡ የደረሱበትን ፡ ለማወቅ ፡ ቸግሮናል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፣ ሕዝበእስራኤል ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ የሙሴን ፡ መጻሕፍት ፡ ዛሬ ፡ በሚገኙበት ፡ አኳኋን ፡ መሰብሰብ ፡ ገና ፡ ሲጀምር ፣ እነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ድሮ ፡ ባገራችን ፡ ነበሩ ፡ ለማለት ፡ ይቸግረናል ።

የጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ከልደተክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ተጀምሮ ፡ ነበር ፡ እንላለን ። ማስረጃው ፡ ግን በጣም ፡ ችግር ፡ ነው ። እርግጥ ፡ የምናውቀው ፡ ክርስቶስ

በተወለደበት ፡ ዘመን ፡ አቅራቢያ ፡ በትግሬ ፡ አውራጃ ፡ ከሐውልትና ፡ ከጸሎት ፡ ቤት ፡ የተጻፈ ፡ አንዳንድ ፡ ቃል ፡ መገኘቱን ፡ ነው ። ቀደምት ፡ የተባሉት ፡ ጽሕፈቶች ፡ የሚገኙ ፡ በሳባና ፡ በግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ከክርስቶስ ፡ ልደት በኋላ ፡ ፫፻ኛው ፡ ዘመን ፡ ሲጀምር ፡ ግን ፣ ጽሕፈቱና ፡ ንግግሩ ፡ የተጣራ ፡ በግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ከሐውልት ፡ ላይ ፡ የተጻፈ ፡ መታሰቢያ ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ ከሊቃውንት ፡ አንዳንዱ እንዲህ ፡ ይላል ፡— የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የጽሕፈት ፡ ቋንቋው ፡ ፊት ፣ ግሪክ ፥ ቀጥሎ ፣ ሳባ ፥ ኋላ ፣ ግእዝ ፡ ኾኑዋል ።

ለዚህ ፡ አሳብ ፡ ብዙ ፡ ተቃራኒ ፡ አልተነሣበትም ። ነገር ፡ ግን ፣ ገና ፡ የመንን ፡ ሳይለቅ ፡ ባገሩ ፡ ቋንቋና ፡ ፊደል ፡ ሲጽፍ ፡ የነበረ ፡ ሕዝብ ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ ሲመጣ ፡ ለምን ፡ በግሪክ ፡ ጻፈ?ደግሞም ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ በቤተክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ የተያዘበት ፡ ሴማዊ ፡ የኾነው ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ እጅግ ፡ የተጣራ ፡ በመኾኑ ፣ ለግሪክና ፡ ለላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ተወዳዳሪ ፡ ሊኾን ፡ ይቃጣዋል ። ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቋንቋ ፡ እያለው ፡ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ጕዳይ ፡ ለምን ፡ በግሪክ ፡ ይጽፋል?የዚህ ፡ ምክንያቱ ፡ እስኪገለጥ ፡ ድረስ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተነገረው ፡ አሳብ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ላይባል ነው ። በርሱ ፡ ፈንታም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚመጣውን ፡ አሳብ ፡ መበገር ፡ ይቻላል ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የጽሕፈት ፡ ቋንቋው ፣ ፊት ፣ ሳባ ፥ ቀጥሎ ፣ ግእዝ ፡ ኑርዋል ። የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ከእስክንድር ፡ ጀምሮ ፡ ሮማዊያን ፡ ግብጽን እስከያዙበትና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እስከብዙ ፡ ዘመን ፡ ለግብጽና ፡ ለታናሽ ፡ እስያ ፡ ሕዝብ ፡ ዋና ፡ ቋንቋ ፡ ኹኖ ፡ ስለነበር ፣ ለኢትዮጵያ ፡ ደግሞ ፡ ከሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ጋር ፡ መገናኛ ፡ ቋንቋ ፡ ኹኖላት ፣ የደብዳቤና ፡ ዐላፊ ፡ አግዳሚ

ከሚያየው ፡ ሐውልትዋ ፣ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ ለሚገበያዩበት
ገንዘብዋ ፡ ይህነንም ፡ ለመሰለ ፡ ልዩ ፡ ጕዳይ ፡ የጽሕፈት ፡
ቋንቋዋ ፡ ኑሮ ፡ ይኾናል ።

በኢትዮጵያ ፡ ከ፩ኛው ፡ መቶ ፡ ዓመተምሕረት ፡
በፊት(ይህ ፡ ማለት ፡ ወንጌል ፡ ባገሩ ፡ ሳይሰበክ) ፡ በሳባ ፡ ኾ
ነ ፡ በግሪክ ፥ በግእዝ ፡ ኾነ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ኑሮ ፡ እንደኾን ፡ ወሬው ፡ ከኛ ፡ አልደረሰም ። ዛሬ
በእጃችን ፡ ያሉት ፡ መጻሕፍት ፣ ከ፩ኛው ፡ እስከ ፡ ሽህ፯፻ኛ
ው ፡ ዓ.ም ፡ በግእዝ ፣ ከዚያ ፡ እስከዛሬ ፡ በግእዝና ፡ በዐማ
ርኛ ፡ የተጻፉ ፡ ናቸው ። ግእዝ ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ መኾኑን
ከዚህ ፡ በፊት ፡ አመልክተናል ። ከዐረብ ፡ በስተደቡብ ፡ ከነ
በሩት ፡ ሴማዊያን ፡ ያንዱ ፡ ነገድ ፡ ቋንቋ ፡ ኑሮ ፡ ይኾናል
ይባላል ። ምናልባትም ፡ ከዚሁ ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ዛ
ሬ ፡ አጋሜ ፡ በምንለው ፡ አውራጃ ፡ ይኖር ፡ ኑርዋል ። ድን
ገት ፡ ደግሞ ፡ ከትግሬ ፡ አውራጃ ፡ ካሉት ፡ ነገዶች ፡ አንዳ
ንዶቹ ፡ ይነጋገሩበት ፡ ኑረው ፡ ይኾናል ። በኢትዮጵያ ፡ ያሉ
ት ፡ የሴም ፡ ቋንቋዎች(ትግርኛ ፥ ትግረ ፥ ዐማርኛ) ፡ ከርሱ
የመጡ ፡ ናቸው ፡ የሚሉ ፡ ሊቃውንት ፡ አሉ ። ይህን ፡ አሳ
ብ ፡ የማይቀበሉ ፡ በዚህ ፡ ፈንታም ፣ ከዐረብ ፡ በስተደቡብ
ሲኖሩ ፡ ከነበሩት ፡ የሴም ፡ ነገዶች ፣ አንዳንዶቹ ፡ ወደ ፡ ኢ
ትዮጵያ ፡ ሲመጡ ፣ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ ኑርዋቸ
ው ፡ የእያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ ቋንቋ ፡ ራሱን ፡ እንደቻለ ፣ በኾ
ነለት ፡ መጠን ፡ እየደረጀ ፡ ኺድዋል ፡ እንጂ ፣ ግእዝ ፡ በ
ኢትዮጵያ ፡ ላለው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሴም ፡ ቋንቋ ፡ አባቱ ፡ አ
ይዶለም ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

በግእዝ ፡ ከተጻፉት ፡ በብዙ ፡ ሽህ ፡ ከሚቆጠሩት
መጻሕፍቶቻችን ፣ ጥቂቶች ፡ ሲቀሩ ፣ ኹሉም ፡ ከክርስቲያ
ናዊ ፡ ግሪክና ፡ ዐረብ ፡ ከሌላም ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐሙ ፡ ና

ቸው ። ደግሞም ፡ የዓለምንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ከሚነግሩት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ ኹሉም ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያዊነታችንን ፡ አሳብ ፡ የሚገልጥ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አይገኝባቸውም ። ዋናው ፡ መጽሐፋችን ፡ ‘መጽሐፍ ፡ ቅዱስ’ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓለምና ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የሠራውና ፡ የሚሠራውን ፡ እስራኤላዊያን ፡ በታያቸው ፡ ዐይነት ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሐፍ ፡ መኾኑን ፣ ኹሉም ፡ ያውቀዋል ። ምስጋና ፡ ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፣ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፣ በያዘው ፡ መንገድ ፡ እየገፋበት ፡ እንዲኼድ ፡ ብርቱ ፡ ኀይል ፡ ተሰጥቶታል ። ደግሞም ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፣ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ወዳገራችን ፡ ሳይመጣ ፡ ገና ፡ ፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ እንደነበረ ፡ በሐተታ ፡ ስንኳ ፡ ብንረዳው ፣ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ጽሑፍ ፡ ምስክሩ ፡ ባላባቶቹ ፡ የጻፉት ፡ መጽሐፍ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ ትርጕም ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ የሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ ለቋንቋው ፣ ለሰዋስው ፡ ማስረጃ ፡ ባላባቶቹ ፡ የጻፉትን ፡ ሲጠቅስ ፣ ግእዝ ፡ ለሰዋስው ፡ ማስረጃ ፡ የሚጠቅስ ፣ ከባዕድ ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐሙትን ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ። በግእዝ ፡ ከጻፉት ፡ ካገራችን ፡ ደራሲያን ፡ ይቅርና ፡ በአሳብ ፥ በአጻጻፍ ፡ ስንኳ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሳይከተሉ ፡ የጻፉ ፡ የሚገኙ ፡ አይመስለኝም ። ይህም ፡ ልምድ ፡ የሃይማኖት ፡ አሳባቸውን ፡ በሚገልጹበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ስለአገራችን ፡ ታሪክና ፡ ማናቸውንም ፡ ጕዳይ ፡ በሚጽፉበት ፡ ጊዜ ፡ ጭምር ፡ ነው ። ይህም ፡ የአጻጻፍ ፡ አካኼድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገንዘብ ፡ ካደረገችው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አሳብ ፡ ጋር ፡ የተስማማ ፡ ንግግር ፡ ለማምጣት ፡ የተ

መቸ ፡ ከመኾኑ ፡ በላይ ፣ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ሳንቀበል ፡ ከነበረብን ፡ አሕዛባዊ ፡ ከኾነ ፡ ምሳሌና ፡ ንግግር ፡ አርቆናል ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነ ፡ አሳብ ፣ ኢትዮጵያዊ በኾነ ፡ ንግግር ፡ የመግለጹ ፡ ዕድል ፡ ለግእዝ ፡ ቀርቶ ፡ ላ ማርኛ ፡ ኹንዋል ።

ዛሬ ፡ ዘመን ፡ በግእዝ ፡ እግር ፡ ተተክቶ ፣ የመን ግሥትና ፡ የሕዝብ ፡ ጕዳይ ፡ የሚሠራበት ፡ የዐማርኛ ፡ ቋን ቋ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዐማርኛ ፡ መጻፍ ፡ ከዠ መረ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኹኖታል ። ዐማርኛ ፡ ከዚ ያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አካሔድ ፡ በ፫ት ዘመን ፡ ቢከፍሉት ፡ ይኾናል ።

፩ኛውን ፡ ዘመን ፣ ዐምደጽዮን ፡ ፲፫፻፵፬–፲፮፻፯(1344-1607)
፪ኛውን ፡ ዘመን ፣ ሱስንዮስ ፡ ፲፮፻፯–፲፮፻፶፭ (1607-1655)
፫ኛውን ፡ ዘመን ፣ ቴዎድሮስ ፡ ፲፰፻፶፭–፲፱፻፵፩(1855-1941)
ቢሉት ፡ ይኾናል ።

ባ፩ኛው ፡ ዘመን ፡ በዐማርኛ ፡ የተጻፈው ፡ ሥራ ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ነው ። የተጻፈውም ፡ ላንዳንድ ፡ ነገሥታት ምስጋና ፡ ደራሲው ፡ ካልታወቀ ፡ የተገጠመ ፡ ቅኔ ፡ ነው ። ቅኔውም ፡ በዘመናት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ እንደምን ፡ ኹኖ ፡ እየተለዋወጠ ፡ ለመኼዱ ፡ ዋና ፡ ምስክር ፡ ከመኾኑ በላይ ፣ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የነገሥታቱ ፡ ሥልጣንና ፡ የተዘረጋ በት ፡ የሰፌው ፡ አገር ፡ ኹኔታ ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፣ ለታ ሪክና ፡ ለዦግራፊም ፡ ማስረጃ ፡ ለመኾን ፡ ይረዳል ። ዐማር ኛው ፡ ዛሬ ፡ ዘመን ፡ የማንናገርበትና ፡ የማንጽፈው ፣ ለማ ስተዋሉም ፡ የሚያስቸግረንና ፡ የሰዋስው ፡ አካኼድ ፡ የተለ ዋወጠ ፡ ብዙ ፡ ቃልና ፡ አገባብ ፡ አለበት ። እርሱን ፡ የመሰ ለ ፡ ዐማርኛም ፡ በየዘመኑ ፡ እየተጻፈ ፡ ምናልባት ፡ እስከ ፡ ፲፮፻፯–፲፮፻፭ ፡ ደርሶ ፡ ይኾናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከ፲፭፻፶፭ ፡ እስከ ፡ ፲፭፻፺፱(1563–1607) ፡ በዐማርኛ ፡ የተጻፈ ፡ ምስክር ፡ አይገኝም ፤ ቢገኝም ፡ ከዚህ ፡ በፊት ያመለከትኹትን ፡ የመሰለ ፡ ግጥም ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ።

ከ፲፭፻ኛው ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ እስላምና ፡ ዐማራው ፡ ወገን ፡ ለይቶ ፡ ዐልጋ ፡ ለመያዝ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ሲዋጋ ፣ በንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ቱርኮችና ፡ ፖርቱጋሎች ፡ በኤርትራ ፡ ባሕር ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ለመዘርጋት ፡ ይፈካከሩ ፡ ነበር ። ቱርኮች ፡ በኤርትራ ፡ ዙሪያ ፡ ላለው ፡ ፖለቲካቸው ፡ የኢትዮጵያን ፡ እስላም ፡ ሲረዱ ፣ ክርስቲያኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተመንግሥት ፡ የፖርቱጋልን ፡ ዕርዳታ ፡ መለመን ፡ ግድ ፡ ኾነበት ። ጀግንነታቸው ፡ የሚመሰገን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ያኽል ፡ ጠመንጃ ፡ የያዙ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ በተዋጉበት ፡ ጊዜ ፣ ድል ለክርስቲያኑ ፡ ወገን ፡ ኾነ ። የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ ግኑኝነት ፡ ሲዠምር ፡ ያገሩ ፡ ካህናት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለማስተማር ፡ እንዲፈቀድላቸው ፡ ተነጋግሮ ነበርና ፡ በስምምነታቸው ፡ የካቶሊክ ፡ ካህናት ፡ በኢትዮጵያ ማስተማር ፡ ዠመሩ ። የሚያስተምሩበትና ፡ የሚጽፉበት ፡ ቋንቋ ፡ ዐማርኛ ፡ ነበርና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተክህነት ፡ ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ ካቶሊክ ፡ እንዳይኾንበት ፡ ግእዝን ፡ ሳይተው በዐማርኛ ፡ መተርጐምና ፡ መጻፍ ፡ ዠመረ ። በዚያው ፡ ዘመን ፡ ለመጻሕፍት ፡ ትርጕምና ፡ ለስብከት ፡ የተጀመረው ዐማርኛ ፡ ገና ፡ ከግእዝ ፡ ነጻ ፡ ያልወጣ ፡ አንዳንዱም ፡ ንግግር ፡ ግእዝ ፡ ላልተማረ ፡ ሰው ፡ በፍጹም ፡ የማይሰማ ፡ ነበር ። እንደዚኸው ፡ ኹሉ ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ ሲጻፍ ፡ የነበረው ፡ የነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ግእዙ ፡ ዐማርኛ ፡ ቅልቅል ፡ ነበር ። ያም ፡ ኹሉ ፡ ኹኖ ፡ እንኳንስና ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ የሚተርፍ ፣ ካገራችን ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ አሳብ ፡ የሚያሳ

ድር ፡ በታረመ ፡ ዐማርኛ ፡ የተጻፈ ፡ መጽሐፍ ፡ ለማግኘት ችግር ፡ ነው ። መጻሕፍቱ ፡ የፈጸሙት ፡ ጕዳይ ፣ በሕዝቡ ላይ ፡ ከመጣበት ፡ ከሃይማኖት ፡ ተወዳዳሪ ፡ መከላከልና ፣ የባላገር ፡ ቋንቋ ፡ የነበረውን ፡ ዐማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ለ ማስያዝ ፡ መዠመራቸው ፡ ነው ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ደራ ሲው ፡ ወይም ፡ ተርጓሚው ፣ ለትሕትና ፡ ሲል ፡ ስሙን ፡ አ ያመለክትም ፡ ነበርና ፡ የመጻሕፍቱን ፡ ፍሬነገር ፡ መዘርዘር ደራሲው ፡ ወይም ፡ ተርጓሚው ፡ ማን ፡ እንደነበር ፡ መርም ሮ ፡ የሕይወቱን ፡ ታሪክ ፡ ማመልከት ፡ አስፈላጊ ፡ ኹኖ ፡ ስ ላልታየን ፡ ትተነዋል ።

ዐማርኛ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባመለከትነው ፡ አኳኋን ሲጎላደፍ ፡ ቆይቶ ፡ ፫ኛ ፡ ብለን ፡ ወደሰየምነው ፡ ዘመን ፡ ይ ደርሳል ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ ፪ኛ ፡ ብለን ፡ ከሠየምነው ፡ አካ ኼድ ፡ በጭራሽ ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፡ ደራሲ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ግእ ዝ ፡ ባልተቀላቀለበት ፡ ዐማርኛ ፡ ብቻ ፡ መጻፍ ፡ የዠመረ አኹን ፡ በቅርቡ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠነገሥት ፡ ፩ ፡ ኀይለሥላ ሴ ፡ ዘመን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ፊተኛ ፡ ኹኖ ፡ ንጹሕ ፡ በ ኾነ ፡ ዐማርኛ ፡ የተጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ የዐጤ ፡ ቴዎድሮስ (፲፰፻፵፯–፲፰፻፷(1855–1868) ፡ ታሪክ ፡ ነው ። ደራሲው ፡ ያጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ጸሓፌ ፡ ትእዛዝ ፡ አለቃ ፡ ዘኑብ ፡ የተባለ ው ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ነው ። የሞተበትን ፡ ዘመን ፡ ማወቅ ፡ አ ልተቻለኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ባ፲፰፻፹ ፡ ዓ.ም ፡ ግድም ፡ ትግ ሬ ፡ ኹኖ ፡ ከንጉሥ ፡ ምኒልክ ፡ ጋር ፡ ሲጻጻፍ ፡ እንደነበር እርግጥ ፡ ነው ። እንደዚኸው ፡ ኹሉ ፣ ባጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ አለቃ ፡ ወልደማርያም ፣ ዐ ጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ታሪካቸውን ፡ በዐማርኛ

ጽፈዋል ። ኹለቱም ፡ ባለታሪኮች ፡ የሚመሰገኑበት ፡ ፊተኞች ፡ ኹነው ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ አጣርተው ፡ በዐማርኛ ፡ መጻፋቸው ፡ ነው ፤ ቃል ፡ ለማሳመር ፡ ስንኳ ፡ ባይጣጣሩ ፣ ግእዝ ፡ ሳይጎትታቸው ፡ ዐማርኛን ፡ ራሱን ፡ እያስቻሉ ፣ ከተፈጥሮ ፡ በተቀበለው ፡ ጠባዩ ፡ አስኪደውታል ። ዐጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አእምሯቸው ፡ በትክክል ፡ ባልሠራበት ፡ ሰዓት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያወረዱት ፡ ጭካኔ ፣ ስላሠቃያቸው ፡ ከ፲፯፻፺፪(1800) ፡ ዓ.ም ፡ ጀምራ ፡ በብዙ ፡ መሳፍንት ፡ ስትገዛ ፡ ለነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡ ንጉሠነገሥት ፡ እንድትስተዳደር ፡ በእርሻና ፡ በንግድ ፣ በትምርትና ፡ በአድሚኒስትራሲዎንም ፡ እንድትሻሻል ፡ የነበረባቸውን ፡ ድካም ፣ ይኸውም ፡ ሥራ ፡ ጀማሪው ፡ እርሳቸው ፡ ኹነው ፣ ለወደፊት ሊከታተሉት ፡ የሚገባ ፡ ሰፊ ፡ ፕሮግራም ፡ መኾኑን ፡ ባለታሪኮቹ ፡ በሚገባ ፡ መጠን ፡ አልተገነዘቡትም ። ስለዚህም ፡ ካጻጻፋቸው ፡ ላይ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ አላጎሉትም ። ግን ደግሞ ፡ በሰላም ፡ መኖርን ፡ ልምድ ፡ አድርጎ ፡ የኖረ ፡ ሕዝብ ፡ ሳያስበው ፡ እንደመብረቅ ፡ መዓት ፡ ያወረደበትን ፡ ንጉሥ ፡ ደግነቱንና ፡ ጨካኝነቱን ፡ ለማመዛዘን ፡ ባይችል ፡ አይፈረድበትም ።

የተወለደበትንና ፡ የሞተበትን ፡ ዘመን ፡ ለማወቅ ያልተቻለ ፡ አለቃ ፡ ዘወልዴ ፡ ባ፲፰፻፺፩(1899)ዓ.ም ፡ አቅራቢያ ፡ ‘ፊተኛይቱና ፡ ኋለኛይቱ ፡ ኢትዮጵያ’ ፡ ብሎ ፡ ሰይሞ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በግእዝና ፡ በዐማርኛ ፡ ታሪክ ፡ ከጻፉት ፡ ደራሲዎቻችን ፡ በተለየ ፡ አስተያየት ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ኹኔታ ጽፍዋል ።

አቶ ፡ ዐጽሜ(+፲፱፻፮/1914) ፡ የሸዋ ፡ ሰው ፡ ናቸው ፤ ስለጋሎች ፡ የጻፉት ፡ ታሪክ ፡ እንግዲህ ፡ ወደአርባ ፡ ዓመቱ ፡ ተቃርቦታል ። ጋሎች ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ የመጡበ

ትን ፡ ዘመንና ፡ አኳኋናቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ በብዙው ፡ ተጣጥረውበታል ። አፈታሪኩን ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ አጣርተውታል ። ደግሞም ፡ በጻፉበት ፡ ዘመን ፡ የኤውሮጳ ፡ ሊቃውንት ፡ ስለጋሎች ፡ ታሪክ ፡ ማጣራት ፡ የጀመሩትን ፡ አንዳንድ ጊዜ ፡ መሠረት ፡ አድርገውታል ። ከኤውሮጳ ፡ ትምርት ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ርቆ ፡ ለሚኖር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከርሳቸው ፡ በበለጠ ፡ አገላለጥ ፡ መጻፍ ፡ ይገባው ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ አይቻልምና ፡ ካገላለጣቸው ፡ አንዳንዱ ፡ ትክክለኛ ፡ ኹኖ ፡ ስንኳ ፡ ባይታይ ፡ የመጽሐፋቸው ፡ ረዳትነት የማይካድ ፡ ነው ። በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ያዲሱ ፡ ትውልድ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ስለነበሩ ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ የነበረባቸው ፡ ቅንዓት ፡ በኦርቶዶክሳዊው ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ባገኙ ፡ ቁጥር ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ የተግሣጽ ፡ ቃል ፡ አስጽፍዋቸዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ታሪኩ ፡ መንገድ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ በኦርቶዶክሳዊያን ፡ ላይ ፡ የኀይል ፡ ቃል ፡ ለመጻፍ ፡ ምክንያቱን ፡ በግድ ፡ ፈልገው ፡ ያመጡት ፡ ይመስላል ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ ባገራችን ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ የባለታሪክ ፡ ስም ፡ የተገባቸው ፡ ደራሲ ፡ ናቸው ።

ኣለቃ ፡ ታየ ፣ (…+፲፱፻፲፯/1924) ፡ በጌምድሬ ፡ ናቸው ። በኢትዮጵያ ፡ ትምርት ፡ ተምረው ፡ የጨረሱትን ፡ ስንኳ ፡ ለማወቅ ፡ ባይቻል ፡ የስብከትና ፡ የድርሰት ፡ ስጦታ ፡ እንደነበራቸው ፡ የታተሙትና ፡ ያልታተሙት ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ይመሰክሩላቸዋል ። እርሳቸውም ፡ ለፕሮቴስታንት ሃይማኖት ፡ ዐዲስ ፡ ምእመን ፡ ነበሩና ፡ የያዙትን ፡ ሃይማኖት ፡ እውነተኛነት ፡ ለማስረዳት ፡ ‘መዝገበ ፡ ቃላት’ ፡ የሚባል ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈዋል ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጦርነት ፡ ያነሡበት ፣ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ የማይስማማ ፡ ኹኖ

የታያቸውን ፣ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣውን ፡ ባገራችን ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህል ፡ እንደዚኸውም ፡ ኹሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በፕሮተስታንት ፡ አካኼድ ፡ ባልተመለከተ ፡ ሊቅና ፡ አዋልድ(አፖክሪፍ) ፡ በምንላቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ ነው ። በመዝገበ ፡ ቃላቱ ፡ እንደአቶ ፡ ዐጽሜ ፡ ያለ ፡ የዘለፋ ፡ ቃል ፡ የለበትም ። ቢኖርም ፡ መጽሐፉ የተጻፈ ፡ ለታሪክ ፡ ሳይኾን ፡ ለሃይማኖት ፡ ማስረጃ ፡ ነውና ፡ ሥፍራው ፡ ነው ፡ ያሰኛል ። መጽሐፉ ፡ ስንኳ ፡ በኦርቶዶክሳዊያን ፡ ላይ ፡ ቢጻፍ ፡ ንግግሩ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ የማያስቀይም ፡ የሊቅ ፡ አነጋገርና ፡ ስለሃይማኖት ፡ ክርክር ለሚጽፍ ፡ ሰው ፡ አብነት ፡ የሚኾን ፡ ነው ።

አለቃ ፡ ታየ ፡ ከጥንት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፲(1918) ፡ ያለውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጽፈዋል ። መጽሐፉ ፡ ባለመታተሙ ፡ ከጥቂቶች ፡ ሊቃውንት ፡ በቀር ፡ የመረመረው ፡ የለም ። መዝገበ ፡ ቃላትና ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ጠላት ፡ አገራችንን ፡ ከወረረው ፡ ወዲህ(፲፱፻፴፮–፲፱፻፵፩/1936–1941) ፡ የደረሱበት ፡ አልታወቀም ።

ሕዝቡ ፡ የሚያነበው ፡ አለቃ ፡ ታየ ፡ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ፡ ከብዙው ፡ በጥቂቱ ፡ የጻፉትን ፡ ነው ። በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ የሚከታተሉት ፡ ፩ኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፣ ፪ኛ ፣ በኢትዮጵያ ፡ ስለታሪክ ፡ የሚናገሩትን ፡ መጻሕፍትና ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ክብረነገሥትን ፣ ፫ኛ ፡ የግሪክን ፥ የላቲንን ፥ የዐረብን ፡ ሊቃውንት ፤ ፬ኛ ፡ በዛሬ ፡ ዘመን ፡ በኤውሮጳ ፡ የተጻፉትን ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ባስተዋሉት ፡ መንገድ ፡ ስለተከተሉት ፡ መንፈሳዊውን ፡ እንጂ ፡ ታሪካዊውን ፡ ጥቅሙን ፡ በጭራሽ ፡ አላገኙትም ። እንደዚሁ ፡ ኹሉ ፡ ክብረነገሥታችንና ፡ የቀሩትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ መጻሕፍት ፡ የግሪክ

ንና ፡ የላቲንን ፡ የዐረብንም ፡ መጻሕፍት ፡ ከኹለት ፡ መቶ
ዓመት ፡ ወዲህ ፡ የኤውሮጳ ፡ ሊቃውንት ፡ አጣርተው ፡ የደ
ረሱበት ፡ ፍጻሜ ፡ ከነወሬው ፡ ሳይደርስላቸው ፡ ቀርቶ ፡ ቃ
ል ፡ በቃል ፡ ተከታትለውታል ። በቅርብ ፡ ዘመንና ፡ ዛሬውኑ
በኤውሮጳ ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ መሠረት ፡ ባለው ፡ አካኼድ ፡
የገለጡትን ፡ ሊቃውንት ፡ ግን ፡ ያንዳንዶቹን ፡ ስንኳ ፡ ስማ
ቸውን ፡ ቢጠሩ ፡ ከነዚሁ ፡ ሊቃውንት ፡ አሳብ ፡ አንድዋ ፡
ከጆሮዋቸው ፡ እንዳልደረሰች ፡ መጽሐፋቸው ፡ ድንቀኛ ፡
አድርጎ ፡ ይመሰክራል ። በሊቃውንቶቹ ፡ ፈንታ ፡ የታሪክ ፡
ሊቃውንት ፡ መስለዋቸው ፡ ከኤውሮጳ ፡ ከዲፕሎማሲና ፡ ከ
ጋዜጣ ፡ መልእክተኞች ፡ ያንዳንዱን ፡ አሳብ ፡ ተከትለዋል ።
ይህ ፡ ኹሉ ፡ ቢኾን ፡ በሃይማኖት ፡ እንዳደረጉት ፣ በታሪክ
እውነት ፡ ኹኖ ፡ በታያቸው ፡ አሳብ ፡ አንዳች ፡ ሥጋት ፡ ሳ
ያድርባቸው ፡ በቅንነት ፡ አሳባቸውን ፡ ያስታወቁ ፡ ሰው ፡ ና
ቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ኀሊናቸው ፡ የተረዳውን ፡ የሚቃወም
ታሪክ ፡ ሲገጥማቸው ፡ ባንደበታቸው ፡ ጥራት ፡ መጠን ፡ ማ
ስረጃ ፡ መስጠትን ፡ ያኽል ፣ 'የልጆች ፡ ጨዋታ ፥ የባልቴት
ተረት' ፡ እያሉ ፡ አልፈውታል ። እንዲህ ፡ ከሚሉት ፡ አብዛ
ኛውንም ፡ ተረት ፡ ነው ፡ ቢሉት ፡ የተገባ ፡ ነው ። ነገርግን
የሚናገርና ፡ የሚጽፍ ፡ ሰው ፣ የማይስማማውን ፡ አሳብ ፡ ተ
ረት ፡ እያለ ፡ ቢኼድ ፣ ሰሚና ፡ አንባቢ ፡ ደግሞ ፡ ማፍረሻ
ውን ፡ አስረዳን ፡ ማለት ፡ እንዳለባቸው ፡ አለመዘንጋት ፡ ነ
ው ፤ እንዲሁም ፡ በታሪክ ፡ ጻፊ ፡ እውነት ፡ ኹኖ ፡ ከሚታየ
ው ፡ አንዳንድ ፡ ለሰሚው ፡ ግራ ፡ ኹኖ ፡ የሚታየው ፡ ይኖር
ይኾናል ። ባለታሪክ ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፣ የሚመታ
ውን ፡ መላ ፡ ወይም ፡ ታሪኩን ፡ የሚመሠርትበትን ፡ ማስረ
ጃ ፡ ማመልከት ፡ ዋና ፡ ሥራው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ፈንታ ፡ አ
ለቃ ፡ ታየና ፡ እስከዛሬ ፡ ከተነሡት ፡ ታሪክ ፡ ጻፎች ፡ አንዳን

ዶቹ ፣ አንባቢው ፡ ባይረዳው ፡ እነርሱ ፡ ለብቻቸው ፡ የተረዱትን ፡ ‘እንደሃይማኖት ፡ ተቀበሉ!’ ፡ ያልተረዱትን ፡ አሳብ ‘እኛ ፡ ተረት ፡ ካልነው ፡ አትቀበሉት!’ ፡ ብለው ፡ የሚያዙ ኹነው ፡ ይታዩናል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ማስረጃ ፡ ብለው ፡ የሚያመጡት ፡ ንግግር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳልኹት የታሪክን ፡ አካኼድ ፡ ያጣሩትን ፡ ሊቃውንት ፡ ሥራ ፡ ዙረው ፡ እንዳላዩት ፡ ንግግራቸው ፡ ያስረዳል ። ይኹን ፡ እንጂ የመጽሐፍ ፡ አካኼድና ፡ መልክ ፡ ላለው ፡ ሥራቸው ፡ ለመጽሐፍ ፡ አጻጻፍ ፡ ንድፍ ፡ በመስጠታቸው ፡ ለአለቃ ፡ ታየና በዚህ ፡ ስማቸውን ፡ ለማነሣቸው ፡ ደራሲያን ፡ ኹሉ ፡ ያገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ባለወረታቸው ፡ ነው ።

አለቃ ፡ ታየ ፡ ወደኤውሮጳ ፡ እየተሻገሩ ፣ ባገራቸውም ፡ ከሕዝባቸው ፡ ማኽል ፡ ኹነው ፡ ሲጽፉና ፡ ሲያስተምሩ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፣ ፊት ፡ ኤውሮጳ ፥ ኋላም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኹነው ፡ ላማርኛ ፡ አጻጻፍና ፡ ንግግር ፡ ብዙ ፡ ትጋት ያሳዩ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ገብረየሱስ ፡ ናቸው ። በወጣትነታቸው ፡ ለትምርት ፡ ወደኤውሮጳ ፡ በመኼዳቸው ፣ በነገር ፡ አስተያየትም ፡ መልክ ፡ ባለው ፡ ንግግር ፡ አሳብን ፡ በጽሕፈት ፡ በመግለጥ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ደራሲ ፡ ናቸው ። የሕይወታቸው ፡ ታሪክ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። የዛሬ ፡ ፶ዓመት ፡ አቅራቢያ ፡ ዕድለኛ ፡ ኹነው ፡ ከጃንሆይ ዐጤ ፡ ምኒልክ ፡ ተመርጠው ፡ ለትምርት ፡ ወደኤውሮጳ ፡ ተላኩ ። የጣሊያን ፡ የጦርአለቃ ፡ ባራቲዬሪ ፡ ፲፰፻፹፰/1896 መልሶ ፡ ወደሮማ ፡ እስኪልካቸው ፡ ድረስ ፣ ከኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡ ጋር ፡ ተሰልፈው ፡ ዐዲግራት ፡ ድረስ ፡ መጡ ። ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ሳትረሳ ፣ ይቅርታ ፡ አድርጋ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽነት ፡ ጊዜ ፡ ለትልቅ ፡ ሥራ ፡ አጨቻቸው ። ለዚህ ፡ ወረታ ፡ ወጣቱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዐልጋ

ወራሽ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ በሚያምር ፡ ንግግር ፡ በማሞገስ ፡ ደስታቸውን ፡ ገለጡ ። በውነትም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ባልኾኑ ካጤ ፡ ምኒልክ ፡ ጋራ ፡ የሠሩት ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ኹሉ ፡ ተቀይመዋቸው ፡ ነበርና ፡ አሳባቸው ፡ የነበረ ፡ በቤተ መንግሥት ፡ ሥራ ፡ ለማስያዝ ፡ ይቅርና ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሬት ፡ እንዳይረግጡ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ባላባቶች ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሥራ ፡ አጀማመር ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ነጻነት ፡ ብዙ ፡ የሚያሠጋ ፡ ኹኖ ፡ ታይቶዋቸው ፡ ሥልጣናቸውን ፡ እንዲያስረክቡ ፡ ባስገደድዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ከዚያ ፡ ኹሉ ፡ ሰው ፡ አብልጠው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የተቈረቆሩ ፡ መኾናቸውን ፡ ለማስረዳት ፣ የሚያምረውን ፡ ግጥማቸውን ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መስደቢያ ፡ በማድረጋቸው ፡ አበላሹት ። እንኳን ፡ ይህን ፣ ከጠላት ፡ ጋር ፡ አገራቸውን ፡ ሊወጉ ፡ የተሰለፉትን ፡ በደል ፡ የቤተመንግሥት ፡ አስተዳደሮች ፡ ትተውላቸው ፡ ነበርና ፣ አኹንም ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱና ፥ ጃንሆይ ፡ ፩ ፡ ኀይለሥላሴ ፡ ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ ኹነው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ ሲያካኺዱበት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፣ ከፍተኛ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተቀበሉ ፤ ከቶውንም ፡ በሚኒስትርነት ፡ ሥራ ፡ ወደሮም ፡ ተላኩ ። ጠላት አገራችንን ፡ ሲያጠፉት ፣ አኹንም ፡ ተመልሰው ፡ ለጣልያን ዋና ፡ ሠራተኛ ፡ ኾኑለት ፤ አገርን ፡ ለያዘ ፡ ጠላት ፡ ሳያስፈልግ ፡ ማገልገል ፡ እንኳ ፡ ከመነቀፍ ፡ ቢያደርስ ፣ ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፡ ለጠላት ፡ ታማኝነታቸውን ፡ ለመግለጥ ፡ አኹንም ፡ ስላገሩ ፡ በሚከላከለው ፡ ላይ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ጀምሮ ፡ እስከተራው ፡ አርበኛ ፡ ድረስ ፡ የማይጠጋውና ፡ ያልኾነ ፡ ቃል ፡ በመጻፍ ፡ ብዕራቸውን ፡ አበላሹ ። ተራ ፡ ጸሐፊ ፡ በኾኑ ፡ የሚያሳዝነውን ፡ የሕይወታቸውን ፡ ታሪክ ፡ ሳላነሣው ፡ በቀረኹ ፤ ነገርግን ፡ ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ እኛ

ላለንበት ፡ ትውልድ ፡ ዋና ፡ ደራሲው ፡ ናቸውና ፡ ለሰው ፡ ከደራሲነቱ ፡ ይልቅ ፡ ስሙንና ፡ ክብሩን ፡ በመጠበቅ ፡ ከኹሉ ፡ የበለጠ ፡ አክሊል ፡ እንደሚገባው ፡ ማስታወስ ፡ ግድ ፡ ይለናል ።

ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ባማርኛ ፡ ከጻፍዋቸው ፡ መጻሕፍት ፣ 'የዐጤ ፡ ምኒልክ ፡ ታሪክ'ን ፥ 'ልብወለድ ፡ ታሪክ' ፡ ዋና ፡ ኹነው ፡ ይታዩናል ። የነርሱን ፡ አኳኋን ፡ ከማስታወቅ ፡ በፊት ፡ የዐማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ሕጉንና ፡ ሕዝቡ ፡ የሚወደውን ፡ የንግግር ፡ ወይም ፡ ያጻጻፍ ፡ ዐይነት ፡ ብናመለክት ፣ ከሕጉ ፡ ርቀው ፡ ዐዲስ ፡ አካኼድ ፡ የሰጡትን ፡ ደራሲያንና ፡ የተለምዶውን ፡ ንግግርና ፡ አጻጻፍ ፡ ሳይለቁ ፡ ጣዕም ፡ ያለበት ፡ ለማድረግ ፡ የቻሉትን ፡ ካልቻሉት ፡ ለመለየት ፡ ይረዳናል ።

የዐማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ከብዙው ፡ ሕግጋቱ ፡ አንዱ ፣ ማሰሪያ ፡ አንቀጽን ፡ ከንግግር ፡ መጨረሻ ፡ ማግባት ፡ ነው ። ከጽሕፈት ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ቃላት ፡ ማኸል ፡ ጣልቃ ፡ እያገባ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳብና ንግግር ፡ በሚጨመርበት ፡ ጊዜ ፡ ዋናውንና ፡ ጣልቃ ፡ የገባውን ፡ ከውኖ ፡ ለማስተዋል ፡ እንዲመች ፡ ሊያደርጉ ፡ የቻሉ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ደራሲያን ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ደራሲው ፡ ሙሉውን ፡ ንግግር ፡ ባማርኛ ፡ ባሕርይ ፡ በሚያስኬድበት ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሰነፍ ፡ አንባቢ ፡ እንዳይታክተው ፡ ለማድረግ ፡ ያሰበበት ፡ እንደኾን ፣ ንግግሩን ፡ ባጭር ፡ ባጭሩ ፡ በማሰሩ ፡ ላንባቢ ፡ መመቸቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ ቢኾንም ፡ ደራሲ ፡ በፊተኛው ፡ (በረጅሙ)አካኼድ ፡ ሲጽፍ ፡ አንባቢው በውጥን ፡ ጭርስ ፡ አካኼድ ፡ አስሮ ፡ ለንግግሩ ፡ ደራሲው ፡ ያላሰበውን ፡ አሳብ ፡ ከመስጠት ፡ የሚደርስበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ደራሲው ፡ በኹለተኛው ፡ አካኼድ(ባጭሩ) ፡ ሲጽፍ ፣ አንባ

ቢው ፡ አኹን ፡ ካመለከትነው ፡ ስሕተት ፡ አይደርስም ፤ ግን ንግግሩ ፡ ባንድ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጽ ፡ ሲጠቀለል ፡ ሲቻል ፣ ደራሲው ፡ እያቋረጠ ፡ በመናገር ፡ አንደበቱ ፡ ያልረታ ፡ ሕፃን ሊመስል ፡ ነው ። ንግግሩም ፡ በመጠኑ ፡ ካማርኛ ፡ ባሕርይ የራቀ ፡ ሊያደርገው ፡ ነው ። ዋና ፡ ደራሲ ፡ የምንለው ፣ በረዥሙም ፡ ኾነ ፡ ባጭሩ ፡ አካኼድ ፡ ጽሮ ፣ ንግግሩ ፡ ግልጽና ፡ ጣዕም ፡ ያለው ፡ ሲኾን ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፣ ሲበዛም ፡ ሲያንስም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ይልቁንም ፡ በምሥራቃዊያን ፡ የተመለደ ፡ አካኼድ ፡ በኹለት ፡ በሦስት ፡ ፍች ፡ የሚተረጐም ፡ ቃል ፡ እየፈለጉ ፡ ከንግግር ፡ ማግባት ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ አካኼድ ፡ ‘ሰማርኛ’ወይም ፡ ‘ስለምን’ ፡ ይባላል (equivoque, jeu de motis, Claortour) ። ይህም ፡ በኢትዮጵያ ፡ እጅግ ፡ የተወደደና ፡ የተለመደ ፡ ንግግር ፡ ኹኖ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ንግግር ፡ የሚያመጣ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የንግግር ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ የሚከራከርበት ፡ አይገኝም ።

ኹለተኛ ፣ በአሳብ ፡ ከልብ ፡ ፈጥሮ ፡ ደጉንና ፡ ክፉውን ፡ በምሳሌ ፡ በሚገልጥበት ፡ ጊዜ ፣ ክፉውንና ፡ ደጉን የሚገልጡትን ፡ ሰዎች ፡ አንባቢው ፡ ወይም ፡ ሰሚው ፡ በተሠራው ፡ ግብራቸው ፡ ባሕርያቸውን ፡ ስንኳ ፡ ቢለይ ፣ ደራሲው ፡ በአሳቡ ፡ የፈጠራቸውን ፡ ሰዎች ፡ ‘አቶ ፡ ክፉ ፡ ሰው’ ፥ ‘አቶ ፡ ደግ ፡ ሰው’ ፥ ‘ወይዘሮ ፡ ዓለሚቱ’ ፥ ይህነንም ፡ የመሰለ ፡ ስም ፡ ይሰይማቸዋል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ አካኼድ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ችክ ፡ ይላል ። ስለኾነም ፡ በደራሲዎችና በሕዝቡ ፡ ተለምድዋል ፤ ተወድዋልም ።

ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፣ ‘ስለምን’ና ‘የምሳሌ ፡ ስም’ ፡ ያልነውን ፡ አካኼድ ፡ በብዙው ፡ አይከተ

ሉትም ። በተከተሉበት ፡ ጊዜም ፡ አንባቢውን ፡ ሳይሰለች ፡ አሳባቸውን ፡ እንዲያስተውል ፡ አድርገዋል ። ሙሉ ፡ ንግግራቸው(Proposition) ፡ ያማርኛን ፡ ባሕርይ ፡ እየተከተለ ፡ በረዘመበት ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፣ ግልጥና ፡ ያማረበት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ቅጽል ፡ ሲያበዙ ፡ ነገሩ ፡ ጉት ፡ ይኾንባቸዋል ። ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ በደራሲነታቸው ፡ ሙቀት ያለበት ፡ ንግግር ፡ ማምጣት ፡ ዋና ፡ ባሕርያቸው ፡ ነው ። ሙቀቱም ፡ የሚገባ ፡ ወይም ፡ ተሽጋጋሪ ፡ በመኾኑ ፣ አንባቢው ፡ አሳባቸውንም ፡ በማይቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ መሞቁ ፡ አይቀርም ። በጽሑፍ ፡ ሥራቸው ፡ የሚያነሡት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ እንሰሳ ፣ ጫካ ፡ ወይም ፡ በረኻ ፡ ኹሉም ፡ ሕይወት ፡ ያለበት ፡ ኹኖ ፡ ይታያል ።

ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ አንድ ፡ ‘የዐጤ ፡ ምኒልክ ታሪክ’ና ፡ አንድ ፡ ‘ልብወለድ ፡ ታሪክ (Roman) ፡ ጽፈዋል ። የቀሩት ፡ በጣልያንና ፡ በፈረንሳይ ፡ ቋንቋ ፡ የጻፍዋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ የዐማርኛን ፡ ሰዋስውና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ኹኔታ ፡ የሚያስታውሱ ፡ ናቸው ።

ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ የዐጤ ፡ ምኒልክን ፡ ታሪክ ሲጽፉ ፣ ንጉሠነገሥቱ ፡ ከደረሰባቸውና ፡ ከሠሩት ፡ ዝርዝር ሳይገቡ ፡ ዋና ፡ ዋናውን ፡ ብቻ ፡ አመልክተዋል ። ጥቂት ፡ ዝርዝር ፡ ያለበት ፡ ስለዐጤ ፡ ምኒልክ ፡ የኢጣልያ ፡ መንግሥት ፡ መልእክተኞች ፡ የሚናገረው ፡ ክፍል ፡ ነው ። የዐጤ ምኒልክን ፡ ታሪክ ፡ ባጭሩ ፡ ካመለከቱ ፡ በኋላ ፡ የጣልያን ፡ መንግሥት ፡ መልእክተኞች ፡ ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅን ፡ እንዲረዱዋቸው ፡ በገንዘብ ፡ ሳይቀር ፡ ሊያባብልዋቸው ፡ እንደሞከሩ ፣ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ሳይታለሉላቸው ፡ በመቅረታቸው የንጉሣቸውን ፡ ፖለቲክ ፡ እንደደገፉ ፡ ለማስረዳት ፡ ይጣጣራሉ ። በንግግራቸው ፡ ለምኒልክና ፡ ለሽዋ ፣ ሲኾን ፡ ቁልም

ጣውንና ፡ ቃለአጋኖውን ፡ ማብዛታቸው ፣ ለሌላው ፡ ወረዳ ባላባትና ፡ ሕዝብ ፡ ሲኾን ፡ ማዋረዳቸውና ፡ መሣቂያ ፡ ለ ማድረግ ፡ መታገላቸው ፣ ለባለታሪክ ፡ የተገባውን ፡ እውነ ተኛ ፡ ሚዛን ፡ የያዙ ፡ በመኾን ፡ ፈንታ ፣ ከዳተኛ ፡ ካለቸቻ ው ፡ አገራቸው ፡ ጋር ፡ ለመቃረብና ፡ የመንግሥቱን ፡ የያ ዙትን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ የተነሡ ፡ ያስመስላቸዋል ። ግን ደግሞ ፡ ከባለታሪክ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ አንዳንዱን ፡ እንዳልዘነጉ ትና ፡ ለታሪክ ፡ ንግግር ፡ ዐዲስ ፡ መንገድ ፡ እንደጠረጉለት ዐጭሩ ፡ የምኒልክ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚያስረዳ ፡ ማስታወቅ ፡ ይ ገባናል ።

'ልብወለድ ፡ ታሪክ' ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሮማን ፡ መ ዠመሪያ ፡ መጽሐፍዋ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳለመለ ከትኹት ፣ ያገራችን ፡ ደራሲ ፡ አሳቡን ፡ በጽሕፈት ፡ ለመግ ለጥ ፡ ባሰበበት ፡ ጊዜ ፡ ባሳቡ ፡ የሚፈጥራቸው ፡ ሰዎች ፡ የግ ብራቸውን ፡ ስም ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ አድርጎ ፡ 'አቶ ፡ መል ካም ፡ ሰው ÷ አቶ ፡ ክፉ ፡ ሰው' ፡ የሚሉትን ፡ አካኼድ ፡ ብ ቻ ፡ ይከታተል ፡ ነበር ። የፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅንና ፡ የኤው ሮጳን ፡ መጻሕፍት ፡ በማንበቡ ፡ ልብወለድ ፡ ታሪክ(ሮማን) ለመጻፍ ፡ ይጣጣራልና ፡ በር ፡ ከፋቹ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አፈወር ቅ ፡ በመኾናቸው ፡ ምስጋና ፡ ይገባቸዋል ።

የፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ልብወለድ ፡ ታሪክ ፡ የሚ ነግረን ፡ የኹለት ፡ ወጣቶችን ፡ ፍቅር ፡ ነው ። ኹሉም ፡ ኢ ትዮጵያዊያን ፡ ኹነው ፣ ሃይማኖታቸው ፡ የወንድየው ፡ እስ ላም ÷ የሴቲቱ ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ። ከኹለት ፡ በፍቅር ፡ ድል ኾኖ ፡ የወዳጁን ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበለ ፡ ወንድየው ፡ ነው ። መጽሐፉ ፡ የፍቅር ፡ ኀይል ፡ ብርቱ ፡ መኾኑንና ፡ የንጹሕ ፍቅር ፡ አካኼድ ፡ እንዴት ፡ መኾን ፡ እንደሚገባው ፡ ከሚ ያስተምረን ፡ በላይ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ ደግሞ ፡ የዛሬ ፡ ሰ

ባት ፡ ወይም ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲደረግ ፡ ከነበረው ፡ ሥራ ፡ ከብዙው ፡ ጥቂቱን ፡ ያመለክተናል ። ደራሲው ፡ የጽሕፈት ፡ አገላለጣቸው ፡ ደግ ፡ ሲኾን ፣ ምክንያት ፡ ለመፍጠር ፡ ብዙ ፡ መንገድ ፡ አልተገለጣቸውም ። ባሳባቸው ፡ የፈጠሩዋቸው ፡ ሰዎች ፡ ለሚፈጽሙት ፡ ኹለት ሦስት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ምክንያት ፡ ሰጥተው ፡ ያንኑ ፡ አንዱን ፡ ምክንያት ፡ ሳይለውጡ ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ደጋግመውታል ። ይህንና ፡ ሌላውን ፡ ብልኀት(የቴክኒክ ጣጣ) ፡ የዋናው ፡ ሥራቸው ፡ ንድፍ ፡ (ፕላን) ፡ ተስተካክሎ ለመኼዱ ፡ አንባቢው ፡ ከሌለ ፡ ይቆጥረዋል ። ይህም ፡ አንድ ፡ ኪነጥበብ ፡ ነው ።

ፕሮፌሰር ፡ አፈወርቅ ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ያኽል ፡ ቲያትር ፡ ጽፈዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እስካኹን ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ በቲያትር ፡ ጨዋታ ፡ አላያቸውም ፤ ደግሞም ፡ አልታተሙም ።

እንደዚሁ ፡ ኹሉ ፣ ብዙ ፡ ደራሲያን ፡ ጽፈው ፡ ያላሳተሙ ፡ አሉና ፡ ሥራቸው ፡ በሕዝብ ፡ ስላልታወቀ ፡ ስለነርሱ ፡ ለመጻፍ ፡ ከዚህ ፡ አይዶለምና ፡ እንተወዋለን ። ቢኾንም ፡ ከነዚህ ፡ ያንዱን ፡ የበጅሮንድ ፥ ተክለሐዋርያትን ፡ ስም ማስታወስ ፡ የተገባ ፡ ነው ። አገራቸው ፡ ሸዋ ፡ የተወለዱበት ፡ ዘመን ፡ ባ፲፰፻፷፰ ፡ ግድም ፡ ነው ። እርሻና ፡ የወታደርነት ፡ ሥራ ፡ በሞስኮብና ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ተምረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሹመት ላይ ፡ ኑረው ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በፓሪስና ፡ በዤኔቭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ሚኒስትር ፡ ኹነው ፡ ነበር ። ፍጹም ፡ ዐማርኛ ፡ በኾነ ፡ ግጥም ፡ ጥቂት ፡ ተረት ፡ ጽፈው ፡ ካሳተሙና ፡ በተረት ፡ ዐይነት ፡ ቲያትር ፡ ከጻፉ ፡ በኋላ ፣ አኹንም ፡ ንጹሕ ፡ በኾነ ፡ ዐማርኛ ፡ ስለዕርሻ ፡ ትምርት ፡ ጽፈዋል ። በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ በዐማርኛ ፡ ቃል ፡ ላልተገኘለት ፡ ለአልኺሚና ፡ ለሌላው ፡ ዕውቀት ፡ የተመረጠ ፡ ቃል

በመገኘቱ ፡ ዕውቀትን ፡ በእውነት ፡ እጅ ፡ ካደረጉት ፡ ለደ
ራሲ ፡ ቋንቋን ፡ እንደልቡ ፡ ማዘዝ ፡ እንደማያስቸግር ፡ ያስ
ረዳል ። በጅሮንድ ፡ ተክለሐዋርያት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕገመ
ንግሥት ፡ መግለጫ ፡ የተናገሩትና ፡ የጻፉት ፡ ደግሞ ፡ የደ
ራሲና ፡ የተሰወረን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ ችሎት ፡ እንዳላቸ
ው ፡ ያስረዳል ።

ነጋድራስ ፡ ገብረሕይወት ፡ ትውልዳቸው ፡ ትግሬ
ኾነው ፡ የሞቱበት ፡ ከዛሬ ፡ ፴ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው ። በልጅ
ነታቸው ፡ ነምሳ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ ተቀምጠው ፡ በትምርታቸ
ው ፡ ሳሉ ፡ ስለዐጤ ፡ ምኒልክና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሐ
ማሴን ፡ ሲታተም ፡ ከነበረ ፡ ጋዜጣ ፡ አሳትመዋል ። 'የመን
ግሥትና ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር' ፡ ብለው ፡ የሰየሙትን ፡
መጽሐፍ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ወዳጆቻቸው ፡ አሳትመዉታል ።
በኹለቱም ፡ ኹሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በሚረዳው
አካኼድ ፡ የቤተመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ መሻሻል ፡ እንዳለበት ፡ ሰ
ብከዋል ። ኹለቱም ፡ መጻሕፍት ፡ ደራሲው ፡ በልበሙሉነት
ስለሚገልጡት ፡ ከፍተኛ ፡ አሳብና ፡ ስለንግግራቸው ፡ ጥራ
ት ፡ በዛሬይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ጉዳይ ፡ ለማሠራትና ፡
ለወደፊት ፣ ሕግንና ፡ ልማድን ፡ እያሻሻሉ ፡ ለማደስ ፡ ስላለ
ብን ፡ ሥራ ፣ ብርቱ ፡ አሳብ ፡ የሚያሳድሩ ፡ የሚያስፈጽሙ
ም ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ሸዌ ፡ ...(ተ፲፱፻፴፱=1939
በባት ፡ ከተማ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ። )በኢትዮጵያ ፡ ከፍተ
ኛውን ፡ ትምርት ፡ ፈጽመው ፡ በቤተክህነት ፡ ሲያገለግሉ ፡
ኑረው ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ በቤተመንግሥት ፡ ልዩል
ዩና ፡ ከፍ ፡ ያለሹመት ፡ ተቀብለው ፡ ከባድ ፡ የኾነ ፡ የኀላ
ፊነት ፡ ሥራ ፡ የፈጸሙ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። የአኹኑ ፡ ማስታ
ወሻ ፡ ስለደራሲነታቸው ፡ ብቻ ፡ የሚናገር ፡ በመኾኑ ፡ በሹ

መታቸው ፡ ስላስኬዱት ፡ ትላልቅ ፡ ሥራ ፡ ከዚህ ፡ ማንሣት
የለብንም ። ከጽሑፍ ፡ ሥራቸውም ፡ ዋና ፡ ኹነው ፡ የሚታ
ዩን ፡ 'ወዳጄ ፡ ልቤ'ና ፥ 'ጎሐ ፡ ጽባሕ' ፡ 'ሀገረ ፡ ጃፓን' ፥
በመኾናቸው ፡ የቀሩት ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ግን ፡ ለኢትዮ
ጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ስንኳ ፡ በብዙው ፡ ቢጠቀሙት ፡ አሳባቸውን
ና ፡ ደራሲነታቸውን ፡ በሦስቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ማግኘት ፡ ስለ
ተቻለ ፡ ስለነርሱ ፡ ብቻ ፡ ባጭሩ ፡ እናመለክታለን ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ በጻፉት ፡ ኹሉ ፡ ዋና ፡ አሳባ
ቸው ፤

፩. በአርኣያ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በ
ፈጣሪውና ፡ በመንግሥት ፡ ዘንድ ፡ አኳያ ፡ መኾኑን ፡ ነ
ው ። የውነት ፡ ነው ። ሲፈጠር ፡ ብልኅና ፡ ሞኝ ፡ ኹን
ዋል ፤ በሥራ ፡ ዕውቀትና ፡ ዕድለኛ ፡ በመኾን ፡ ከሰው
የተሠራ ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነ ፡ የመዐርግ ፡ ከፍተኛነትና
ዝቅተኛነት ፡ ይህንንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ልዩነት ፡ አለ ።
ነገር ፡ ግን ፡ በምንፈርድለትና ፡ በምንፈርድበት ፡ ጊዜ
መሠረት ፡ ልናደርገው ፡ የሚገባነ ፡ ኹሉም ፡ ትክክል
መኾኑን ፡ ነው ።

፪. በዘርና ፡ በሃይማኖት ፡ የመጣውን ፡ ልዩነትም ፡ እርስ
በርሳችን ፡ ተቻችለን ፡ ከሌለ ፡ መቍጠር ፡ ይገባናል ።

፫. የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዓለም ፡ ከታወቁት ፡ ሃይማኖቶ
ች ፡ ለመንፈሳዊና ፡ ለሥጋዊ ፡ ኑሮ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ።

፬. ሰው ፡ በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ ሞት ፡ እንደሚመጣበት
ማሰብ ፡ ይገባዋል ።

፭. ሰው ፡ የልማድ ፡ ባሪያ ፡ ሳይኾን ፡ በነጻነት ፡ ሕጉንና ፡
ሥርዐቱን ፡ እያሻሻለ ፡ መኼድ ፡ አለበት ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ከጻፍዋቸው ፡ መጻሕፍት ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ዕድለኛ ፡ ኹኖ ፡ ሕዝቡ ፡ አንብቦ ፡ የማይ ጠግበው ፡ ‘ወዳጄ ፡ ልቤ’ን ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ መ ጽሐፍ ፡ የሚጽፍ ፡ የእንግሊዙን ፡ ደራሲ ፡ የዮሐንስ ፡ ቡንያ ንን ፡ መጽሐፍ ፡ ያነበበ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ የምንረዳ ው ፡ የዚሁኑ ፡ ደራሲ ፡ ‘የክርስቲያን ፡ መንገድ’ ፡ የተባለው ን ፡ መጽሐፉን ፡ ስናነብ ፡ ነው ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ግ ን ፡ ንድፉን(ፕላኑን) ፡ ስንኳ ፡ ከእንግሊዙ ፡ ደራሲ ፡ ቢቀበሉ የጽሑፋቸውን ፡ ሕንጻ ፡ መልክና ፡ ጠባይ ፡ በፍጹም ፡ ኢትዮጵ ያዊ ፡ ያውም ፡ የሚያምር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አድርገውታል ።

ባሳባቸው ፡ የፈጠሩት ፡ ‘ወዳጄ ፡ ልቤ’ ፡ የተባለው ሰው ፡ የርሳቸው ፡ ራሳቸው ፡ ወይም ፡ የክርስቲያንን ፡ ሕግ ለመጠበቅ ፡ የሚታገል ፡ ሰው ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። ወዳጄ ፡ ል ቤ ፡ ለብቻው ፡ ኹኖ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ህላዌና ፡ የሕዝበ አዳምን ፡ በተለይም ፡ የነፍስን ፡ ኹኔታ ፡ በሚያስብበት ፡ ጊዜ ፣ ወይም ፡ እግር ፡ ጥሎት ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ተገና ኝቶ ፡ ክፋታቸውንና ፡ በጎነታቸውን ፡ በሚገልጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በተለይም ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ የሚመጣበትን ፡ መከራ ፡ ሲያስታውስ ፣ ተስፋ ፡ ሲቆርጥ ፡ ሲቃጣና ፡ በርትቶ ፡ ሲታገል ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ጋርና ፡ ለብ ቻው ፡ መሰንቆውን ፡ ይዞ ፡ ሲያንጐራጕር ፣ በሰርግ ፡ አስ መስሎ ፡ ስለክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ አዠማመርና ፣ ድል እየነሣ ፡ በኼደበት ፥ በሚኼድበትም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ያለበ ትን ፡ መከራ ፡ ሲተርክ ፣ ፍጹም ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ነው ።

‘ወዳጄ ፡ ልቤ’ ፡ ‘ሰው ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካመ ነ ፡ በኋላ ፡ ከኀጢአት ፡ ላይ ፡ ላለመውደቅ ፡ ምን ፡ ቢሠራ ይሻላል?’ ፡ ብሎ ፡ የሚጠይቅ ፡ ወይም ፡ የዚህን ፡ አሳብ ፡ የሚያሳድር ፡ ኹኖ ፡ ይታያል ። አንባቢው ፡ ቍልፉን ፡ ወይም

መልሱን ፡ አገኘኹ!መጽሐፉ ፡ ሊነግረኝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲ ጓጓ ፣ 'ብፁዐን ፡ እለ ፡ ተኃድገ ፡ ሎሙ ፡ ኃጢአቶሙ' ፡ ብሎ ፡ ያሰናብተዋል ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ስለሃይማኖትና ፡ ስለፖለቲክ ፥ ስለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጕዳይም ፡ ያሰቡትን ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ሰብስበው ፡ ጽፈው ፡ ያወጡትን ፡ መጽሐፍ ፡ 'ጎሐ ፡ ጽባሕ' ፡ ብለው ፡ ሰይመውታል ። ጎሐ ፡ ጽባሕ ፡ ስለሃይማኖት የሚገልጠው ፡ አሳብ ፣ ንግግሩም ፡ ልዩ ፡ ቢኾን ፡ ከወዳጄ ልቤ ፡ አይለይም ። ሕግንና ፡ ልማድን ፡ ማሻሻል ፡ ብላቴን ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ የቆሙበት ፡ ዋና ፡ ሐሳብ በመኾኑ ፥ ስለቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቊጥር ፣ ስለምንኵስናና ፡ ስለጋብቻ ፡ ሥርዐት ፥ ስለጸሎትና ፡ ስለንስሐ ፡ ከጻፉት ክፍል ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖት ፡ ሥርዐት ፡ እየተሻሻለ ፡ የሚኼድበትን ፡ መንገድ ፡ መሠረት ፡ ባለው ፡ አካኼድ ፡ አስረድተዋል ። ከቤተክህነት ፣ ቤተመንግሥትን ፡ መምራት ይገባኛል ፡ እያለ ፣ በመነፈሳዊውና ፡ በሥጋዊው ፡ ጕዳይ ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ልኹን ፡ የሚል ፡ እንደማይጠፋ ስለተረዱት ፡ የኹለቱንም ፡ ሥልጣን ፡ ወስነው ፡ ኹሉም ፡ በየክፍሉ ፥ በየሥራው ፡ አላፊነት ፡ እንዳለበት ፣ የኹሉ ፡ የበላይ ፡ ግን ፡ መንግሥት ፡ መኾኑን ፡ አደላድለው ፡ ወስነዋል ። ወገን ፡ ለሌለው ፥ በዘር ፡ በሃይማኖት ፡ ለተለየ ፡ ሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ ርኅራኄ ፡ እንዲገባ ፡ በብዙው ፡ ሰብከዋል ። ለዛሬው ፡ ትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አንዳንዱ ፡ ስንኳ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ምክር ፡ ባያስፈልገው ፡ ካገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ላብዛኛው ፡ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ ኹኖ ፡ ታይቶት ፡ ከአሳባቸው ፡ አንዳንዱ ፡ ለመቀበል ፡ የሚያስቸግር ፡ ኹኖ ፡ ሳይታየው ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፣ መጽሐፉ ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ ብር

ቱ ፡ አሳብ ፡ የሚያሳድርበትና ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ የ
ሚያስነሣ ፡ ነው ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ገና ፡ ወደጃፓን ፡ የመንግ
ሥት ፡ መልእክተኛ ፡ ኹነው ፡ ሳይኼዱና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡
ከኢትዮጵያ ፡ ውጭ ፡ ስላይዋቸው ፡ አገሮች ፡ ኹኔታ ፡ የጻፏ
ቸው ፡ መጻሕፍት ፡ አሉ ። በተስተካከለ ፡ ዐማርኛና ፡ ያላዩ
ትን ፡ አገርና ፡ ሕዝብ ፡ ካዩት ፡ በሚያስቈጥር ፡ አነጋገር ፡
የመንገዳቸውን ፡ አኳኋን ፡ የገለጡበት ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡
'ማኅደረ ፡ ብርሃን'(ሀገረ ፡ ጃፓን) ፡ ብለው ፡ የሰየሙት ፡ ነ
ው ። መጽሐፉ ፡ ከማያስፈልግና ፡ ከሚያታክት ፡ ዝርዝር ፡
ሳይገባ ፡ በወሬ ፡ የምናውቀው ፡ የጃፓን ፡ አገርና ፡ ሕዝቡ ፣
ሃይማኖቱ ፣ ያገሩ ፡ ልማድ ፣ ሥልጣኔውና ፡ አስተዳደሩ ፡
ምን ፡ እንደኾነ ፡ ነግሮ ፡ የሚያጠግብ ፡ ነው ። ደራሲው ፡ የ
ተላኩበት ፡ ሥራ ፡ ከሕዝብና ፡ ከትላልቅ ፡ ሰው ፥ ከንጉሠነ
ገሥትና ፡ ከንግሥቲቱ ፡ ጋር ፡ የሚያገናኝ ፡ በመኾኑ ፣ የሆ
ቴሉንና ፡ የባላገሩን ፥ የሚኒስትሮቹንና ፡ የቤተመንግሥቱን
ዕልፍኝ ፡ ታዳራሽ ፡ ወጉንና ፡ ሥርዐቱን ፡ አይተዋል ። ከዚህ
ም ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ መኾን ፡ ከዠመረበት
ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ታሪኩን ፡ እ
ንድናውቀው ፡ ከሌላ ፡ ባለታሪክ ፡ እየጠቀሱ ፡ ባጭሩ ፡ ተርከ
ውልናል ። የባሕሩንና ፡ የመሬቱን ፣ የጫካውን ፡ ኹኔታ ፡ የ
ሚነግረው ፡ ክፍል ፣ ደኅና ፡ ሥዕል ፡ ሣይ ፡ በሚስማማ ፡ ቀ
ለም ፡ ነድፎ ፡ ያቀረበው ፡ ሠሌዳ ፡ ይመስላል ። ክርስቲያኑ
ኅሩይ ፣ ክርስቲያን ፡ ያይደሉትን ፡ ወገኖች ፡ አምልኮና ፡ ባሀ
ል ፡ የሚያዩት ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። የጃ
ፓን ፡ አምልኮም ፡ እንደሌላው ፡ አምልኮ ፡ የእግዚአብሔርን

ምስጢር ፡ ለማግኘት ፡ የሚጣጣር ፡ ኹኖ ፡ ስለታያቸው ፣ ያገራችን ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ ባይቀበለውም ፡ በሰፊው ፡ እንዲመለከተው ፡ አድርገው ፡ ገልጠውታል ።

ከዚያ ፡ በፊት ፡ ልዩልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ በመጻፍ ፡ ብዙ ፡ ትግል ፡ ያየው ፡ የብላቴን ፡ ጌታ ፡ አእምሮ ፡ ዐማርኛ ፣ ሀገረ ፡ ጃፓንን ፡ በጻፈበት ፡ ጊዜ ፣ ደርጅቶ ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ደረጃ ፡ የደረሰ ፡ ኹኖ ፡ ይታያል ።

ዐማርኛ ፡ ማሰሪያ ፡ አንቀጹን ፡ አርቆ ፡ ከማኽሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳብ ፡ ጣልቃ ፡ ማስገባት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ነው ፡ ብለናል ። ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ይህን ፡ ሳይከተሉ ፡ ንግግሩን ፡ ባጭር ፡ ባጭሩ ፡ ማሰር ፡ ልዩ ባሕሪያቸው ፡ ነው ። ከዐማርኛ ፡ መርማሮች ፡ አንዳንድ ፡ ሰው ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ዐማርኛን ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ (በኤውሮጳ) ፡ ንግግር ፡ ዐይነት ፡ እንጂ ፡ በተፈጥሮ ፡ ጠባዩ አያስኬዱም ፡ ብሎ ፡ ጽፎባቸዋል ። ነገሩም ፡ እውነት ፡ ይኾናል ፤ ግን ፡ ደግሞ ፡ ደራሲ ፡ መከተልና ፡ ማሻሻል ፡ የሚገባው ፡ የሚጽፈበትን ፡ ቋንቋ ፡ ጠባይ ፡ ነው ፡ ስለተባለ ፣ ይኸው ፡ ደራሲ ፡ የሚጽፈው ፣ የንግግር ፡ ጣዕም ፡ ያለውና ፡ በፍጥነት ፡ የሚያስተውሉት ፡ ከኾነ ፣ ከተራው ፡ ሕዝብ ፡ ተለይቶ ፡ ማዕርግ ፡ ያለው ፡ ደራሲ ፡ ነው ፡ መባልን ፡ አያግደውም ።

ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ለሕፃናትና ፡ አእምሮ ፡ ለዋጭ ፡ የሚኾኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መጻሕፍት ፡ ትተውልናል ። እንዲያውም ፡ ከመጻሕፍት ፡ ዐይነት ፡ በጽሕፈት ፡ በመግለጥ ፡ ያልሞከሩት ፡ ጥቂት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ። በሥራ የተፈነው ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕሪያቸው ፡ ትዕግሥተኛ ፡ ሲኾን ፣ ጽሕፈት ፡ ሲልዋቸው ፡ ፍጥነታቸው ፡ የመኪና ፡ ያኽል ፡ ስለነበረ ፣ ካማርኛቸው ፡ በቀር ፣ ለወጣቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ላ

ንዳንዱ ፡ የጻፉት ፡ ታሪክና ፡ ልብወለድ ፡ ታሪክ ፥ ሌላውም
ኹሉ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ውዝፍ ፡ ኹኖ ፡ ይታየዋል ። ም
ክንያቱም ፡ በቤተመንግሥት ፡ የነበረባቸው ፡ ከባድ ፡ ሥራ ፣
ለሚጽፉት ፡ መጽሐፍ ፡ የተገባውን ፡ ምርመራ ፡ ለማጥለቅ
ና ፡ ለማስፋፋት ፡ ፋታ ፡ አልሰጣቸው ፡ ስላለና ፡ ላገራቸው
ሕዝብ ፡ በነበረባቸው ፡ ፍቅር ፣ እርሳቸው ፡ ካወቁት ፡ ከብ
ዙው ፡ ጥቂቱን ፡ ሳያስታውቁት ፡ ቢቀሩ ፡ ‘ዘደፈነ ፡ ወርቅ ፡
እግዚኡ’ ፡ እንዳይኾኑ ፡ ሲሉ ፡ ይኾናል ። የሒሳብና ፥ የፍል
ስፍና ፡ የሕክምና ፡ የሥነፍጥረት ፡ ይህንም ፡ የመሰለው ፡ ል
ዩልዩ ፡ ዕውቀት ፡ የተጻፈበትን ፡ ጽሑፍ ፡ ሥራ ፡ ቋንቋው
የተጣራ ፡ ቢኾን ፡ ያንኑ ፡ ዕውቀት ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ካልኾ
ነ ፡ በቀር ፣ በሌላ ፡ ዕውቀትም ፡ ሊቅ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ አያስተ
ውለውም ። የድርሰት ፡ ስጦታቸው ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ግ
ን ፣ እንኳንስና ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ተራው ፡ ሕዝብ ፡ ሳይቀር
በሚያስተውለው ፡ ንግግር ፡ ልዩ ፡ ዕውቀታቸውን ፡ ለመጻፍ
ተችልዋቸዋል ። ቃለእግዚአብሔር(theologie) ፡ የሚያስተም
ሩና ፡ የሃይማኖትን ፡ መጻሕፍት ፡ የሚተረጕሙ ፥ ስለሃይ
ማኖትም ፡ የሚጽፉት ፡ ሊቃውንት ፣ ምስጢሩ ፡ ግድ ፡ እያ
ላቸው ፡ ንግግራቸው ፡ ወይም ፡ አጻጻፋቸው ፡ ዐማርኛ ፡ ዐ
ወቅኹ ፡ ለሚል ፡ ኹሉ ፡ የማይደፈር ፡ ኹኖ ፡ ይኖራል ። ደ
ግምም ፡ ትምርት ፡ ሲባል ፡ ከጥንት ፡ እስከዛሬ ፥ ያገር ፥ የ
መንግሥት ፡ ወሰን ፣ የማያግደው ፡ አገሩና ፡ መንግሥቱም
ቢለያዩ ፡ ሰንደቅዓላማው ፡ ወይም ፡ ወገኑ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡
ነው ። ለጊዜው ፡ ያገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ወደ
ውጭ ፡ ያለው ፡ ትምርትና ፡ ዕውቀት ፡ ባዕድ ፡ ኹኖባቸዋል ።

　　　　አለቃ ፡ ኪዳነወልድ ፡ ክፍሌ ፡ ትውልዳቸው ፡ ሸዋ ፣
ትምርታቸው ፡ ጐንደር ፡ ነው ። ዕድሜያቸው ፡ ፸፫ዓመት

ይኾናል ። በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ካላቸው ፡ ከሰፊው ፡ ዕውቀታቸው ፡ በላይ ፣ ላገራችን ፡ መጻሕፍት ፡ ምስጢርና Sens ታሪክ ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነውን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ዕብራይስጥ ፡ ጨምረውበታል ። የሕዝቅኤልን ፡ ትንቢት ፡ ዕብራይስጡን ፡ ወደዐማርኛ ፡ ገልብጠው ፡ ባማርኛ ፡ የጨመሩበት ፡ መግለጫ ፣ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ ላገራችን ፡ ሊቃውንት ፡ ከግሪክ ፡ ተተርጕሞ ፡ በግእዝ ፡ ተቀብለውት ፡ የሚኖሩትን ፡ የብሉያትን ፡ መጻሕፍት ፣ ዋናውን ፡ አብነት ፡ ዕብራይስጡን ፡ እያዩ ፡ ማቃናት ፡ እንዳለባቸው ፡ አነቃቅተዋቸዋል ። ዳግመኛ ፡ ትምርቱም ፡ መጠነኛ ፡ ቢኾን ፥ ዐማርኛ ያወቀ ፡ ኹሉ ፡ ሊያስተውለውና ፡ ሊያጣጥመው ፡ በሚችል ንግግር ፡ በመግለጣቸው ፡ ተራውን ፡ ሕዝብ ፡ ሳይቀር ፡ ከሊቃውንቱ ፡ ዕውቀት ፡ እንዲካፈል ፡ አድርገውታል ። እግረመንገዳቸውንም ፡ ልዩ ፡ ለኾነው ፡ ከባድ ፡ ዕውቀት ፣ ልዩ የኾነና ፡ ያጌጠ ፡ ዐማርኛ ፡ ፈጥረውለታል ። እርሳቸው ፡ ከዛሬ ፡ ሠላሳ ፡ ዐመት ፡ በፊት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኼደው ፡ ዕብራይስጥ ፡ በተማሩበት ፡ ዘመን ፡ የነበረውን ፡ ችግር ፡ ያስተዋለ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ድካማቸውን ፡ ሊመዝነውና ፡ ሞያቸው ትልቅ ፡ መኾኑን ፡ ሊረዳው ፡ ይችላል ። ፍቅርና ፡ አንድነት በተሰበከበት ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ጠብና ፡ መለያየት ፡ ተዘርቶበት ፡ ነበር ። ዛሬውንም ፡ ገና ፡ አላለፈለትም ። ከዚያ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መነኮሳት ፡ ማኅበር ፡ ከጸሎት በቀር ፣ ትምርት ፡ መቀጠል ፡ የማያስፈልግ ፡ ሥራ ፡ ኹኖ ሲታየው ፣ እስራኤላዊ ፡ ደግሞ ፡ በዓለም ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ዐሥር ፡ ቢማር ፡ እንደማያፈቅረው ፡ ተረድቶት ፡ ቋንቋውን ሊማርለት ፡ የመጣውን ፡ ክርስቲያን ፡ መርዳት ፣ እባብን ፡ ከመቀለብ ፡ ይቈጥረው ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ወልድ ፡ ዕብራይስጥ ፡ የተማሩት ፡ በኹለት ፡ ፊት ፡ ሥቃያ

ት ፡ እያዩ ፡ ነው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ድካማቸው ፡ በክርስቲያን ሊቃውንት ፡ ጭምር ፡ ስለብሉያት ፡ መጻሕፍትና ፡ ታሪክ ፡ ያመጡትን ፡ ዐዲስ ፡ መግለጫ ፡ ለመከታተል ፡ ቢቸግራቸው ፣ ዐማርኛው ፡ ከተሰናዳው ፡ መግለጫቸውም ፡ በክርስቲያንነታቸው ፡ የጸኑት ፡ ሊቃውንት ፡ ከደረሱበት ፡ የታሪክና የትርጒም ፡ ዐዲስ ፡ አካኼድ ፡ ለመድረስ ፡ ቢያቅታቸው ፡ አይፈረድባቸውም ።

የኢትዮጵያን ፡ የጥንቱን ፡ ትምርት ፡ ከሚያውቁት ሊቃውንት ፡ ዐማርኛንና ፡ ግእዝን ፡ ለማጣራት ፣ ያለቃ ፡ ኪዳነወልድን ፡ ያኽል ፡ የሚደክም ፡ ብዙ ፡ አልተገኘም ። ዐማርኛ ፡ ለግእዝ ፡ ልጁ ፡ በመኾኑ ፣ ከግእዝ ፡ የተቀበላቸውን ፡ ቃላት ፡ ልክ ፡ እንደግእዝ ፡ አድርጎ ፡ መያዝ ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ስላለባቸው ፣ ይህንኑ ፡ ውሳኔ ፡ ለመግለጥ ፡ የታተመና ፡ ያልታተመ ፡ ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈዋል ። አሳባቸውን ፡ ተቀብለሎም ፡ ለማስቀበል ፡ የሚጣጣር ፡ በያገሩ ፡ ብዙ ፡ ደቀመዝሙር ፡ አውጥተዋል ። ሠላሳዓመት ፡ ያኽል ፡ የደከሙበት ፡ ዋናው ፡ መጽሓፋቸው ፡ ግእዝን ፡ ባማርኛ ፡ የሚተረጒም ፡ መዝገበ ፡ ቃላት(Dictionnaire) ነው ። ጠላት ፡ አገራችንን ፡ በወረረበት ፡ ዘመን ፡ እርሳቸው ፡ ሲታሰሩ ፡ ሲጋዙ ፣ ያን ፡ ያኽል ፡ የደከሙበትን ፡ ሥራየሚከውነው ፡ አጥቶ ፣ የብልና ፡ የምስጥ ፡ ምግብ ፡ ኹኖ ፡ መቈነጻጸሉ ፡ ጉዳቱ ፡ የራሳቸውና ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ወሰን ፡ ሳያግደው ፡ ሰንደቅዓላማ ፡ ሳይለየው ፣ ወገን ለኾነው ፡ በዓለም ፡ ላለው ፡ የትምርት ፡ ወዳጅ ፡ ለኾነው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ነው ። ከሰው ፡ ተለይተው ፣ ፈቃድ ፡ አጥተው ፡ ሲኖሩ ፡ ሳለ ፣ ዕውቀታቸውን ፡ እንዲያካፍሉ ፡ ከችግር አስጥለዋቸው ፡ የነበሩ ፡ ንጉሠነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለሥላሴ ፡ ናቸው ። ዛሬም ፡ ንጉሠነገሥታችን ፡ የኢትዮጵያን ፡

ዐልጋ ፡ መልሰው ፡ ሲይዙ ፣ አለቃ ፡ ኪዳነወልድን ፡ አስፈልገው ፡ የዕለት ፡ እንጀራቸውን ፡ በመዐርግ ፡ እንዲያገኙና ፡ ያቋረጡትን ፡ ሥራ ፡ እንዲዠምሩ ፡ አድርገዋልና ፡ ፈቃዱ ኹኖ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ የግእዝን ፡ ቋንቋ ፡ ከሥር እስከመሠረቱ ፡ ለማወቅ ፡ ከገዛ ፡ አገራቸው ፡ ሊቅ ፡ በተጻፈው ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ይመረምሩታል ፡ እያልን ፡ ተስፋ እንደርጋለን ።

በግጥም ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ሳይመታ ፣ ቃሉ ፡ ያላጋደለ ፣ የተመዛዘነ (Rythmique) በኾነ ፡ ንግግር ፡ አሳብን ፡ መግለጥ ፣ ሰው ፡ አንደበት ፡ ከፈታ ፡ ዠምሮ ፡ የነበረ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በጽሕፈት ፡ ያልገባው ፡ ያገራችን ፡ የጥንት ፡ ወግና ፡ ታሪክ ፣ ብዙ ፡ ግጥም ፡ አለበት ። ሌላ ፡ የቀድሞ ፡ ሕዝብ ፡ የቤተመንግሥቱን ፡ ሕግ ፡ ሳይቀር ፡ ቤት ፡ እያስመታጽፎ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ በዜማ ፡ እንዲማሩት ፡ አድርጓል ። በኢትዮጵያ ፡ ማናቸውንም ፡ የግእዝ ፡ ስንኳ ፡ በዜማ ፡ ማንበብልምድ ፡ ቢኾን ፣ ሕግን ፡ በግጥም ፡ መጻፍ ፡ አልተለመደም ። ነገር ፡ ግን ፡ ቤት ፡ የሚመታ ፡ የሕግ ፡ ዐይነት ፡ ምሳሌ አይጠፋም ። ‘ይካስ ፡ የበደለ ፥ ይሙት ፡ የገደለ’ ፣ ‘ያባት ዕዳ ፡ ለልጅ ፥ ያፍንጫ ፡ እድፍ ፡ ለእጅ’ ፣ ‘አልሞት ፡ ባይ ፥ ተጋዳይ’ ። ይህንም ፡ የሚመስል ፡ ባንድ ፡ ፊት ፡ ምሳሌ ፣ እግረመንገዱን ፡ ደግሞ ፡ ሕግ ፡ ኹኖ ፡ የሚጠቀስ ፥ ቤት ፡ የሚመታ ፡ ብዙ ፡ ንግግር ፡ አለ ። በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሳሽና ፡ ተከሳሽ ፡ ተከራክረው ፡ ሲጨርሱ ፥ ዐጭር ፡ ኹኖ ፡ ቤት ፡ በሚመታ ፡ ንግግር ፡ ጉዳያቸውን ፡ ለዳኛ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ። ከትች ፡ ላይ ፡ ዛሬውንም ፡ ቢኾን ፡ በግጥም ፡ የሚተች ፡ አለ ፤ የበገናና ፡ የመሰንቆ ፡ ልዩልዩ ፡ ዝማሬ ፥ ባላገሩ ፡ ለአምላክና ፡ ለድንግል ፡ ማርያም ፥ ለመልአክና ፡ ለጻድቅ ፡ የሚያቀርበው ፡ ልመናና ፡ ምስጋና ፡ በግ

ጥም ፡ ነው ። ቀረርቶና ፡ ዘፈን ፣ እንጕርጕሮሽና ፡ ልቅሶ ፡ ኹሉም ፡ በግጥም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ልዩልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ አስቀድሞ ፡ ቤት ፡ እየመታ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ በተወ ሰነ ፡ ሚዛን (Rythmie) አሳቡን ፡ የሚገልጥበትን ፥ ጽሑፍ ሥራው ፡ ሲደራጅ ፡ ባገራችን ፡ ጽሑፍ ፡ ሥራ (Litterature) ግጥም ፡ የኋሊት ፡ ቀርቱዋል ። ስለኾነም ፡ አኹን ፡ በቅርቡ ጊዜ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በግጥም ፡ መጻፍ ፡ ዠምረዋል ። አብዛኛው ፡ ስላልታተመ ፡ ስለዐማርኛ ፡ ግጥምብዙ ፡ የምና መለክተው ፡ የለነም ። ያሳተሙትና ፡ ያላሳተሙት ፡ ያማር ኛ ፡ ቅኔዎች ፡ በግጥም ፡ የሚገልጡት ፡ አሳብ ፡ አብዛኛውን ምክር ፡ ነው(didactique) ። የሰውን ፡ ሐዘንና ፡ ደስታ ፡ የሚ ገልጠው(poesie lyrique)እጅግ ፡ በጥቂቱ ፡ ኹኖ ፣ የወንድ ንና ፡ የሴትን ፡ ፍቅር ፡ የሚያነሣ ፡ በጭራሽ ፡ የለበትም ። የ ጣልያኖች ፡ ወረራ ፣ ስለአገርና ፡ ስለንጉሠነገሥት ፡ ፍቅር ፣ ዐመፀኝነት ፥ ስለሚሠራበት ፡ ግፍ ፥ ስለነጻነትም ፡ ናፍቆት በግጥም ፡ የሚያናግር ፡ አሳብ ፡ ቀስቅሰዋል ። የተጻፈው ፡ ገ ና ፡ ስላልተመረመረ ፣ የሚያምረውን ፡ ከማያምረው ፡ ለ መለየት ፡ ለጊዜው ፡ አልተቻለም ። ስለዐማርኛ ፡ የቅኔ ፡ ባ ሕርይ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ ብዙ ፡ 'ስለም ን' ፡ ወይም ፡ 'ዐማርኛ'(Calembour jeu de mots) ይወዳል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አያሌውን ፡ መሥመር ፡ Vers ባንድ ፡ ፊደል (lettre, syllable) ቤት ፡ ያስመታል (Monorime) ። አንዱን ፡ መሥመር (vers) በኹለት ፡ ሐረግ (hemstiche) ከፍሎ ፡ ላንዳንዱ ፡ ሐረግ ፡ ፮ ፥ ለኹለቱ ፡ ሐረግ (ላንዱ መሥመር) ፡ ፲፪ ፡ ፊደል ፡ ይሰጣል ። ፊደል ፡ ሲቆጥር ፡ አ ብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እንደዕብራይስጡ ፡ ቅኔ ፡ ሳድሱን ፡ ከሌለ ፡ ይቆጥረዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በአሳቡና ፡ በንግግሩ ፡ ስንኳቅኔ ፡ ወዳጅና ፡ ቅኔ ፡ ፈጣሪ ፡ ኹኖ ፡ ቢታይ ፣ ባማርኛ ፡ እስከዛሬ ፡ ጽፈው ፡ ካሳተሙት ፡ ግጥም ፡ ገጣሚዎች ፣ ትዕግሥት ፡ ሰጥቶዋቸው ፣ ሽኽ ፡ መቶ ፡ መቶ ፡ ሽኽ ፡ መሥመር ፡ የጻፉና ፡ ያሳተሙ ፡ ያሉ ፡ አይመስለንም ። በርከት ፡ አድርገው ፡ የጻፈ ፡ ቢኖርባቸው ፡ ለፍርድ ፡ ይመች ፡ ነበር ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ ዐጭርም ፡ ቢኾን ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ሥራቸውን ፡ የማደንቅላቸውና ፡ የማመሰግንላቸው ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ አሉ ። ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ከበደ ፡ ሚካኤል ፡ ነው ። ቅኔ ፥ ምሳሌ ፥ ተረት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ደራሲ(ከፈረንሳይ) ፡ በሚተረጕምበት ፡ ጊዜ ፡ አሳቡና ፡ ንግግሩ ፡ ዐማራ ፡ ኹኖ ፡ ከተረጐመበት ፡ ቋንቋ ፡ ጋራ ፡ ሲያስተያዩት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ተወዳዳሪው ፣ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ አርሞ ፡ ያቃናው ፡ ኹኖ ይገኛል ። ምክንያቱን ፡ ከራሱ ፡ አፍልቆ ፡ በሚፈጥረው ፡ ግጥም ፡ ከልብ ፡ የወጣ ፡ ከልብ ፡ ይገባል ፡ እንደተባለው ፡ ኹሉ ፡ ልብን ፡ የማይነካ ፡ የሚገኝበት ፡ ኹኖ ፡ አልታየኝም ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ካገራችን ፡ ባለቅኔዎች ፡ ግእዝን ፡ ወይም የውጭ ፡ አገርን ፡ ቋንቋ ፡ እጅ ፡ ያደረጉ ፡ ሲኾኑ ፣ ወደዚያው ፡ እየሳባቸው ፡ ንግግራቸውን ፡ ለማስተዋል ፡ እንቸገርበታለን ። ወይም ፡ ደግሞ ፣ ሌላ ፡ ባለግጥም ፡ ያወጣውን ፡ ንግግር ፡ ዐማርኛው ፡ ካማረ ፡ ብለው ፡ ያለቦታው ፡ ሲጥሉት ቅር ፡ ያሰኛሉ ። ‘ስለምን’ ፡ የልኹትን ፡ ንግግር ፡ አምጥተው ፡ አንባቢ ፡ በተሎው ፡ እንዳያስተውለው ፡ ያደረጉ ፡ እንደኾን ፡ ሰው ፡ ሊያስተውለው ፡ ያልቻለ ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ የተገለጠላቸው ፡ ይመስላቸዋል ። ከበደ ፡ ሚካኤል ፣ ሌሎች ፡ ካበጁት ፡ ወይም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ንግግር ፡ ሳይጨምር ፡ በራሱ ፡ ዐማርኛ ፣ ዐማራ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ሊያስተውለው ፡ የሚችል ፡ አገላለጥ ፡ በመምረጡ ፡ ለወደፊት ፡ ለሚነ

ሡት ፡ ያማርኛ ፡ ባለቅኔዎች ፡ አብነታቸው ፡ ለመኾን ፡ ተስፋ ፡ የሚያስደርግ ፡ ልጅ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ተስፋ ፡ ስለዐማርኛ ፡ ደራሲያን ፡ ከብዙው ፡ ጥቂቱን ፡ ያስታወስነውን ፡ መጨረሳችን ፡ ነው ። ለንግግራችን ፡ ፍጻሜ ፡ ስንሰጥም ፡ ደግመን ፡ የምናስታውስው ፡—

፩. በዐማርኛ ፡ መጻፍ ፡ ከዠመርነ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ስንኳ ፡ ቢኾን ፡ በብዙው ፡ የተጻፈበት ፡ ዘመን ከ፲፱፻ ዓ.ም. በኋላ ፡ መኾኑን ፣

፪. ካ፲፱፻ዓ.ም.ዠምሮ ፡ በዐማርኛ ፡ የሚጻፈው ፡ አብዛኛው ፡ የሃይማኖት ፡ መጽሐፍ ፡ ኹኖ ፡ ከንግግሩና ፡ ከአሰካኩ ፡ ከግእዝ ፡ ነጻ ፡ ያልወጣ ፥ ብዙ ፡ አካኼድ ፡ እንደነበረበት ፥ ይህም ፡ የአጻጻፍና ፡ የንግግር ፡ አካኼድ ፡ ዛሬውን ፡ ሳይቀር ፡ አንዳንድ ፡ ጸሓፊዎች ፡ እንደሚከተሉት ፣

፫. ዐማርኛ ፡ ራሱን ፡ አስችለው ፡ መጻፍ ፡ የዠመሩት ፡ ደራሲያን ፡ በዐጤ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዘመን ፡ ፲፰፻፵፯–፲፰፻፷ መኾኑን ፣ ጭራሽ ፡ እየተጣራ ፡ የኼደበት ፡ ግን ፡ በኀይለሥላሴ ፡ ዘመን ፡ መኾኑን ፣

፬. ዐማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ሥራውን ፡ በግጥም ፡ ዠምሮ ፥ ይኸው ፡ የግጥም ፡ ሥራ ፡ ዛሬ ፡ የኋሊት ፡ መቅረቱን ፣

፭. የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ደራሲያን ፡ ከሚጽፉት ፡ አብዛኛው ፡ መጽሐፋቸው ፡ የታሪክና ፥ የሃይማኖት ፥ የልብወለድ ታሪክም ፡ መኾኑን ፣ የኹሉም ፡ አሳብ ፡ ትምርትን ፡ ሥራንና ፡ ልማድን ፡ እያሻሻሉ ፡ መኼድ ፡ ዋና ፡ መኾኑን ፣

፮. የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍጥረቱ ፡ የቅኔ ፡ መንፈስ ፡ ያደረበትና ፡ በግጥም ፡ አሳቡን ፡ እንደገለጠ ፡ መኖሩን ፣ ሙግቱንና ፡ ትቹን ፡ ሳይቀር ፡ በግጥም ፡ ማምጣት ልማዱ ፡ መኾኑን ፣ በዚህኛውም ፡ የተፈጥሮ ፡ ልማዱ ቤት ፡ እያስመታ ፡ የሚኼድ ፡ ደራሲ ፡ በብዙው ፡ መገኘቱን ፥ ነገርግን ፡ በዐማርኛ ፡ ያወጣውን ፡ ግጥም ፡ ያሳተመ ፡ ደራሲ ፡ ጥቂት ፡ መኾኑን ፡ ነው ።